# አዲስ ዘመን

እናድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 156 የካቲት 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢትዮጵያን የስንዴ ኤክስፖርት አስጀመሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያን የስንዴ ኤክስፖርት አስጀመሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀደም ሲል "ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት ራሷን በመቻል ስንዴን ከውጭ ማስገባት ማቆም ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት በትኩረት ይሰራል" ባሉት መሰረት በትናትናው ዕለት በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በመገኘት የስንዴ ኤክስፖርት አስጀምረው በአጭር ጊዜ ውስጥ ቃልን ወደ ተግባር ቀይረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዳዩን አስመልክተው በማሕበራዊ ትስስር ገጻቸው፤ ለሕዝባችን የተናገርነውን በተግባር ፈጽመን የኢትዮጵያን የስንዴ ኤክስፖርት እውን አድርገናል" በማለት ስኬቱን አብስረዋል።

"እኛ የምናልም፣ ያለምነውን የምንናገር፣ የተናገርነውን ሌት ከቀን የምንሰራ፣ የሰራነውን ደግሞ አጠናቅቀን የምናሳይ ስለመሆናችን ማረጋገጫ ነው" በማለትም ቃል ወደ ተግባር መቀየሩን አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በተጓዳኝ የኤክስፖርት መጠን በመጨመር ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። በተለይም ለበጋ መስኖ ስንዴ የተሰጠው ትኩረት እነሆ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍሬ ማፍራት መጀመሩ ትልቅ ስኬት ሆኗል።

በስንዴ ኤክስፖርት መርሀ-ግብሩ ላይ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እና የክልሉ አመራሮች ተገኝተዋል።

## በመዲናዋ በግማሽ ዓመቱ 412 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች ተከናውኗል

- ከ360 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ጥገና ሥራዎች ተሰርተዋል
- ክፍለ ከተሞች ወሰን የማስከበር ሥራ እንዲሰሩ ጥሪ ቀርቧል

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን በልዩ ልዩ የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች 442 ኪሎ ሜትር በላይ በስድስት ወር ውስጥ ለማከናወን ታቅዶ 411 ነጥብ 9 ኪሎ ሜትር በማከናወን የእቅዱን ከ93 በመቶ በላይ ማሳካቱን ገለጸ።

የባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ እያሱ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት ከ360 ኪሎ ሜትር በላይ የተለያዩ የመንገድ ጥገና ሥራዎች እንዲሁም ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከመንገድ ግንባታ ሥራዎች አኳያ በተወሰነ መልኩ የአፈጻጸም ድክመት እንደነበር የገለጹት ዳይሬክተሩ ለዚህም ዋነኛውና አንዱ ምክንያት የወሰን ማስከበር ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ችግር በመሆኑ ነው ብለዋል።



ችግሩን ለመፍታትና የተሻለ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በበጀት ዓመቱ በርካታ የወሰን ማስከበር ስራዎች ቢከናወኑም ከታቀደው አኳያ የተወሰኑ መጓተቶች በመኖራቸው ከወሰን ማስከበር በኩል ድርሻ ያላቸው ክፍለ ከተሞች በተሻለ ደረጃ ወሰን የማስከበር ሥራውን

በመዲናዋ በግማሽ ዓመቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ክልሉ በውሃ ፓምፖች የሚለማውን መሬት ወደ 20 ሺህ ሄክታር ለማሳደግ እየሠራ ነው

- 20 ሺህ የሚጠጉ የውሃ ፓምፖች በሥርጭት ላይ ናቸው

መክሊት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በውሃ ፓምፖች የሚለማውን መሬት ወደ 20 ሺህ ሄክታር ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሆልቲካልቸር ዳይሬክተር አቶ ይበልጣል ወንድምነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ30 እስከ 40 ሺህ የሚደርሱ የውሃ ፓምፖችን በመጠቀም ከዚህ ቀደም በክልሉ 14 ሺህ ሄክታር ይለማል፡፡ ተጨማሪ 20 ሺህ የሚጠጉ የውሃ ፓምፖች ወደ ስራ እንዲገቡ እንየተደረገ ሲሆን ይህ የውሃ ፓምፖች ሥርጭት በክልሉ ውስጥ ይለማ የነበረውን የመሬት መጠን ወደ 20 ሺህ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ከግብርናና እና የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በጋራ በመሆን ለአርሶ አደሩ የውሃ ፓምፖችን የማሰራጨት ሥራው እየተከናወነ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ይበልጣል፤ መንግሥት የውሃ ፓምፖችን በማሰራጨት ለግብርናው ዕድገት የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡

በውሃ ፓምፕ ሥርጭቱ ሳቢያ ከፍተኛ ሄክታር

ክልሉ በውሃ ፓምፖች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



















ዜና

# "የኢትዮጵያ የውሃ ማማነት ከመሬት አቀማመጥ አንጻር እንጂ ከሚፈለገው የውሃ ፍላጎት ጋር የሚገናኝ አይደለም"

## * የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት 47 በመቶ ደርሷል ፣ 53 በመቶ ፍላጎት አለ

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር
ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፦ ኢትዮጵያ ባላት ውሃ ልክ እና ለልማት ከሚፈልገው የውሃ መጠን አንጻር ኢትዮጵያ ብዙ ውሃ የሚያስፈልጋት ሀገር እንጅ የውሃ ማማ አይደለችም ሲሉ የውሃ ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ሀብታሙ ኢተፋ ገለጹ። በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት መረጃ መሰረት በተያዘው በልግ የዝናብ እጥረት ሊከሰትባቸው በሚችሉ ቦታዎች ውሃ ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ የኢንስቲትዩቱን መረጃ መሰረት በማድረግ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለልማት ስራዎች ከሚያስፈልጋት የውሃ ፍላጎት አንፃር አሁን ያላት በቂ አይደለም፤ በድርቅ ብዙ ዜጎች የሚፈናቀሉባት ፣ ድርቅ በየዓመቱ የሚከሰትባት ሀገር ናት። የኢትዮጵያ የውሃ ማማነት ከመሬት አቀማመጥ አንጻር እንጂ ከሚፈለገው የውሃ ፍላጎት ጋር የሚገናኝ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል። ዛሬም ቢሆን ድርቅ እየተፈራረቀብን ነው ፣ የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በተያዘው በልግ በአንዳንድ አካባቢዎች ከመደበኛ በታች ዝናብ መጠን ይጠበቃል።

ኢንስቲትዩቱ ህብረተሰቡና መንግሥት ችግሮች ከመድረሳቸው በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ያግዛል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በትንበያው መሰረት የዝናብ እጥረት በሚከሰትባቸው አካባቢዎች ውሃ ለማድረስ ዝግጅት ላይ ነው። መካከለኛ እና ለመደበኛው ተቀራራቢ ዝናብ መጠን የሚያገኙና የተገኘውን ውሃ


ፎቶ - ኢዮብ ተፈራ

በአግባቡ እንዲጠቀሙ እንዲሁም እጥረት የሚገጥማቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የኢንስቲትዩቱን መረጃ ለሁሉም አካላት የማድረስ ሥራ እየተሰራ ነው ብለዋል ።

ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች በምዕራብ ፣ በደቡብ ምስራቅ መካከለኛ እና ብዙም ስጋት ላይ የማይጥል የዝናብ መጠን ይጠበቃል። በደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ እና ሰሜን ምስራቅ ሀገሪቱ ክፍሎች አካባቢ ትንሽ ዘግይቶ እንደሚገባ ገልጸዋል።

መረጃ ማድረስ ቀዳሚ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ስራ ነው ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ዘግይቶ በሚገባባቸው አካባቢዎች ቦረና ፣ ሶማሌና ሌሎችም ክፍሎች አካባቢ መረጃውን ቶሎ ለኅብረተሰቡ እንዲያደርሱ የሚመለከታቸው ፌዴራል እና ክልል ተቋማት በተለይ ግብርና ሚኒስቴር፣ ክልል ግብርና ብሮ፣ ውሃ እና አካባቢ ጥበቃ የማድረስ ስራዎች እየተሰራ ነው። በቀጣይ ውሃ እጥረት የሚከሰትባቸውን አከባቢዎች ውሃ የማድረስ እና የተገኘውን ውሃ እንዴት መጠቀም እንዳለበት አስፈላጊውን ዝግጅት እየተደረገ ነው ።

እንደ ዶክተር ሀብታሙ ገለጻ ፤ በተቀናጀ መልኩ ስራውን ለማሳካት በግብርናው ዘርፍ በተፋሰስ ልማት እና የአረንጓዴ አሻራ ልማት ስራዎችን ማጠናከር ለቀጣይ ስራዎች ግብዓት ይሆናሉ። የውሃ እጥረትን ለመከላከል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለኤሌክትሪክ እና ለመስኖ ልማት ከግድቦች ውሃን የማከፋፈል ሥራ በትኩረት ይሠራል ብለዋል። 47 በመቶው አቅርቦት እና 57 በመቶ ሃይል አቅርቦት ሽፋን ለኅብረተሰቡ ቀሪ የቤት ስራ እንደሆነ አያይዘው ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት እስከ አሁን በአረንጓዴ አሻራ ልማት 25 ቢሊዮን የተተከሉ ችግኞ እና የተፋሰስ ልማት ስራዎች የውሃ አካላት መጠናቸው እንዲጨምር አድርጓል ብለዋል።

ሀይቆችን ከማልማት አንጻር የውሃ አካላት ደህንነት እየተሰራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ አብዛኞቹ ሃይቆች በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ስለሚገኙ ሃይቆችን ለማልማት በሃይቁ ዙሪያ የሚገኙ የሰው ሀብት መሰረት በማድረግ ለሀይቆች ማስተር ፕላን መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዋናነት ውሃ ሳንቴሽን እና ኢነርጂ ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ ጠቁመው መረጃውን መሰረት በማድረግ ዝናብ እጥረት በማይከስትባቸው አካባቢዎች የተገኘውን ውሃ በአግባቡ መጠቀም አለበት።

# በጋምቤላ ክልል በ139 ሄክታር የተጀመረው የበጋ ስንዴ ልማት ውጤታማነቱ ታይቷል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ 139 ሄክታር ላይ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ውጤታማ መሆኑን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አጃክ ኡቻላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የበጋ ስንዴ ልማት እንደ ተሞክሮ በመውሰድ በጋምቤላ ክልል ወደ ልማቱ ስራ የተገባ ሲሆን የተገኘው ውጤትም አበረታች ነው።

በዚህ ዓመት 480 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ለማልማት የታቀደ ሲሆን በሦስት ወረዳዎች 139 ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም እየለማ እንደሚገኝና



የተወሰኑ ባለሀብቶችም በሙከራ ደረጃ ማልማታቸውን ተናግረዋል።

አራት ሺህ 170 ኩንታል ስንዴ ከበጋ መስኖ ልማቱ እንደሚጠበቅ የተናገሩት አቶ አጃክ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ውጤት በጋምቤላ ክልል ስንዴ ማልማት እንደማይቻል የሚነገሩ መላምቶችን የሚያስቀር እና በቀጣይ የበለጠ ለመስራት የሚያነሳሳ ነው ብለዋል።

አቶ አጃክ እንደሚሉት፤ የበጋ ስንዴ እየለማ የሚገኘው ከመስኖ በተጨማሪ ውሃ ከሚገኝበት አካባቢ የውሃ መሳቢያ በመጠቀም ነው። በክልሉ በበጋ መስኖ የስንዴ ልማቱ ስራ በሙከራ ደረጃ ቢሆንም በኅብረተሰቡ ዘንድ ተነሳሽነት ፈጥሯል። አርሶ አደሩ በኩታ ገጠም በመስራት በአንዳንድ አካባቢዎች ምርት መሰብሰብ መጀመሩንም ተናግረዋል።

የግብርና ባለሙያና የትራክተር እጥረት፣ የውሃ መሳቢያዎች በቂ አለመሆን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ስራ ተግዳሮቶች መሆናቸውም ተብራርቷል።

ለቀጣዩ የመኸር ወቅት ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ ጠቁመው ከበጋው ስንዴ በበለጠ በመኸሩ ይሰራል ተብሎ እንደታሰበ ገልጸዋል።

# የኢትዮጵያ አይሁዲዎች የሀገራቱን ግንኙነት በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አይሁዲዎች የእስራኤልንና የኢትዮጵያን ግንኙነት በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ስለመሆናቸው በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አስታወቁ።

በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል በርካታ የጋራ ፕሮጀክቶች አሉ። ቤተ እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በርካታ ስራዎችን እየሰሩ ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱ በቅርቡ የሰው ማጓጓዣ አውሮፕላንን ወደ ካርጎ (የእቃ ማመላለሻነት) የመቀየር ስራ ተሰርቷል።

በተመሳሳይ የዓባይ ግድብ ግንባታን ለማገዝ ቦንድ መግዛታቸውንና እርዳታ መስጠታቸውን የገለጹት አምባሳደሩ፤ ኅብረተሰቡንም የኢትዮጵያን ባህል፣ አመጋገብ፣ አለባበስና አጋጊያጥ ሁሉንም ነገር እንደሚያስተዋውቁ ገልጸዋል።

በእስራኤል ያሉ የኢትዮጵያ አይሁዲዎች በህክምናው ዘርፍም በርካታ ዶክተሮችና አንደኛ ደረጃ ነርሶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እገዛ


አምባሳደር አለልኝ አድማሱ

ያደርጋሉ ብለዋል። በጸጥታው ዘርፍም ከኢትዮጵያ የሄዱ ወጣቶች ሰልጥነው ከፍተኛ ደረጃ በመድረስ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትብብር ስራዎች እየተሰሩ ነው።

በዚህ ዓመት ጥምቀትን በጎንደርን ማክበር በሚለው መርሃ ግብር ለመሳተፍ ከሰባት ሺህ በላይ እስራኤላውያንና የኢትዮጵያ አይሁዲዮች መጥተዋል። ይህም ሁለቱን ሀገራት የሕዝብ ለሕዝብና ግንኙነትን በከፍተኛ ሁኔታ እያጠናከረ ነው። ወደ አውሮፓና ኤዥያ ከመሄድ ይልቅ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት እንደሚወዱ ገልጸዋል።

ለተፈናቀሉ ዜጎች የኢትዮጵያ አይሁዲዮች ድጋፎችን አሰባስበው መላካቸውን አብራርተዋል። ለፈረሱ ጤና ጣቢያዎችና ትምህርት ቤቶችም መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አበርክቶ እንዳላቸው አብራርተዋል።

ኢትዮጵያን ሲከፋት የሚደሰት እስራኤላዊ የለም የሚሉት አምባሳደር አለልኝ፤ በመንግሥት ደረጃ የነበረው ግንኙነት መውረድና መውጣት ሲያጋጥመው የሕዝቡ ግንኙነት ሁልጊዜም ጠንካራ ነበር። በዚህም ጥሩ የሆነ ግንኙነት አለ፤ ይህም እየተጠናከረና እየተስፋፋ ነው ብለዋል።

አምባሳደር አለልኝ እንደገለጹት፤ እስራኤል በዲፕሎማሲ መስክ የኢትዮጵያን ድጋፍ ትፈልጋለች። ይህን በተመለከተ በጋራ መስራት ያስፈልጋልም ሲሉ አክለዋል።



# "የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በጥናትና ምርምር የተደገፈ ሥርዓተ ትምህርት መፍጠር ያስፈልጋል"

- ፈቀደ ቱሊ(ዶ/ር)
በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር ያጋጠመንን የትምህርት ጥራት ችግር ለመቅረፍ በእውቀት የሚመራና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በተገቢው የሚጠቀም ሥርዓተ ትምህርት መፍጠር እንደሚያስፈልግ በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪው ፈቀደ ቱሊ(ዶ/ር) ገለጹ።

የአገሪቱ ትምህርት ጥራት ችግር እንዳለበት የዘንድሮው የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ውጤት ትልቅ ማሳያ ነው ብለዋል።

ዶክተር ፈቀደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014 ዓ.ም የ 12ኛ ክፍል ፈተና የተመዘገበው ውጤት አስደንጋጭና የትምህርት ሥርዓታችን ችግር ውስጥ መሆኑን በደንብ አሳይቷል። በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍ በእውቀት የሚመራና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በደንብ የሚጠቀም የትምህርት ሥርዓት መፍጠር የግድ ሆኗል።

በትምህርት ጥራት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ብሎም ስብራቱን መልሶ ለመጠገንም ጊዜ ይፈልጋል ያሉት ተመራማሪው፤ የትምህርት ሥራ የሁሉንም ባለድርሻዎች ትብብርና ርብርብ እንደሚጠይቅ አብራርተዋል።

ተመራማሪው አክለው እንደገለጹት፤ ሥርዓተ ትምህርቱና የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱ ሊፈተሽ ይገባል፤ የቀድሞው የፈተና አሰጣጥ ሂደቱም የፈተና ወረቀት ወጥቶ ለተማሪዎች የሚታደልበት ወቅት እንደነበር አውስተዋል።

አሁን ለተመዘገበው ውጤት ክብደቱ ይለያይ እንጂ ሁሉም ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት ጠቅሰው፤ በዚሁ መሰረት መንግሥት፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና ወላጆችም ለትምህርት ጥራት መውረድ የየድርሻቸውን አሉታዊ ሚና አበርክተዋል ነው ያሉት።

አገር ለምታለች የምንለው ሰው ሲለማ መሆኑን ያመለከቱት ዶክተር ፈቀደ፤ ሁሉም ሴክተር ከትምህርት ጋር የተያያዘ ስለሆነ የሚስተዋለውን የሙስና ብልሹ አሰራር፣ የፍትሕ መጓደልና በሌሎችም አገልግሎት መስጫ ዘርፎችና ሙያዎች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከትምህርት ዘርፉ ችግር ጋር የሚያያዙ ናቸው ብለዋል።

ከትምህርት ጥራት ችግሩ ባለፈ ኮቪድ 19 እና የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የነበሩ የፀጥታ ችግሮችም ዘርፉን በትልቁ እንደጎዱት አንስተው፤ በብዙ ነገሮች ድምር የመጣውን ችግር ከማራገብ ባለፈ መፍትሔው ላይ አተኩሮ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የተሻለ የትምህርት ሥርዓት የገነቡ አገራት በትምህርት ጥራትና በመምህራን ብቃት ላይ የተሻለ ሥራ በመስራታቸው መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ፈለቀ በመምህርነት ሙያ ላይ በደንብ መሠራት አለበት ብለዋል።

ትምህርትን እንደ ኢንቨስትመንት በመቁጠርም ለትምህርት ዘርፉ የሚመደበውን በጀት ማሳደግ፣ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበው፣ የወላጅና ትምህርት ቤትን ግንኙነትን ማጠናከርና ወላጆች ልጆቻቸውን የሚከታተሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣ የትምህርት አመራሮችን አቅም እና የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሳደግና በዘርፉ ተጠያቂነትን ማስፈን የሚሉትን ጉዳዮች በመፍትሔነት አንስተዋል።

ዜና



አቶ እንድሪስ ገመቹ

# በባቱ ከተማ ከግብርና ምርቶች ከ565 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኘ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ ባለፉት ስድስት ወራት ከግብርና ምርት ከ565 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንደተገኘ የባቱ ከተማ ግብርና ክላስተር ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የከተማው ግብርና ክላስተር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ እንድሪስ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በባቱ ከተማ ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ ከወተት፣ ከስጋ፣ ከዶሮ፣ ከእንቁላል፣ ከማር እና ከዓሳ ምርት ከ565 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

እንደ አቶ እንድሪስ ገለፃ፤ በባቱ ከተማ ከአትክልትና ፍራፍሬ 200 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ እስከ አሁን ድረስ 120 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል። ከወተት ምርት ከ 151 ሚሊዮን ብር በላይ ለማግኘት ታቅዶ እስከ አሁን ከ 100 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት የተቻለ ሲሆን በዶሮ ምርት ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ ለማግኘት ታቅዶ በስድስት ወራት ውስጥ ከ19 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

በተመሳሳይ በእንቁላል ምርት ከ 184 ሚሊዮን ብር በላይ ለማግኘት ታቅዶ እስከ አሁን ከ148 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘት የተቻለ ሲሆን በማር ምርት ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ለማግኘት ታቅዶ በግማሽ ዓመቱ ሦስት ሚሊዮን ብር ማግኘት እንደተቻለ ኃላፊው ተናግረዋል።

አቶ እንድሪስ እንደተናገሩት፤ በባቱ ከተማ በግማሽ ዓመቱ ከወተት፣ ከዶሮ፣ ከእንቁላል እና ከማር ምርት ከ277 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል። ይህም በከተማው የስራ ዕድል ፈጠራን በማበረታታት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ያጠናክራል። ከዚህም ባለፈ የከተማው ነዋሪዎች ራሳቸውን በምግብ እንዲችሉ ያደርጋል።

የግብርናው ዘርፍ የሥራ ዕድል በመፍጠርና ኑሮን ለማሻሻል፣ ለኢንዱስትሪዎች በቂ የጥሬ ዕቃ ግብዓት ለመሆን፣ ለወጭ ንግዱ በቂ ምርት በአይነት፣ በብዛትና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ሰፊ ዕድል እንዳለው ይታወቃል። ስለዚህ በከተማዋ የኩታገጠም እርሻን በመጠቀም በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው።

ኢትዮጵያን ማሳደግ ማለት የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ኑሮ መቀየር እንደሆነ የጠቀሱት አቶ እንድሪስ፤ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው ተናግረው፤ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ተወዳድራ ልታመጣ ከምትችለው ውጤት በላይ በግብርናው ዘርፍ ማሸነፍ የምትችልበት ዕድል መኖሩን ተናግረዋል።

በግብርና ምርታማነት ላይ መስራቱ አዋጭ እንደሆነ አመልክተው፤ ለዚህም የባቱ ከተማ ግብርና ክላስተር ጽህፈት ቤት ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ ከወተት፣ ከስጋ፣ ከዶሮ፣ ከእንቁላል፣ ከማር እና ከዓሳ ምርት የሚገኘውን ምርት ለማጠናከር አቅጣጫ ይዞ መንቀሳቀስ ጀምሯል። የተገኘው ገቢም የዚህ አንዱ አካል ነው ብለዋል።

# ሸበሌ ባንክ ቀጣናውን በፋይናንስ ተጠቃሚነት የማስተሳሰር አቅም እንዳለው ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ጅግጅጋ፡- በሶማሌ ክልል የተቋቋመው ሸበሌ ባንክ የምስራቅ አፍሪካ ቀጣናን በፋይናንስ ተጠቃሚነት የማስተሳሰር አቅም እንዳለው ተገለጸ።

የሸበሌ ባንክ አገልግሎት ማስጀመሪያ ሥነ-ሥርዓት በጅግጅጋ ከተማ ተከናውኗል። በወቅቱ በሶማሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር አብዱልፈታ አብዱልአዚዝ እንደገለጹት፤ ሸበሌ ባንክ ከኢትዮጵያ አልፎ በጎረቤት አገራት አገልግሎት መስጠት የሚችልበት አማራጭ ስላለው የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነቱን ለማስፋት ትኩረት ማድረግ አለበት።

ባንኩ የሚሰጣቸው የተለያዩ ከወለድ ነጻ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሸሪዓን ሕግጋት የተከተሉ በመሆናቸው በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና አገራት ውስጥ የሚገኙ ከወለድ ነፃ ባንክ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማሟላት ያስችለዋል። በዚህ ረገድ በሶማሊያና በሌሎች ጎረቤት አገራት ጭምር አገልግሎቱን ለማቅረብ መዘጋጀት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የፋይናንስ ተቋማት ድንበር ተሻጋሪ ሥራዎችን በማከናወን የቀጣናው ኢኮኖሚያዊ ትስስር የበለጠ እንዲጠናከር ማድረግ ይችላሉ። ሸበሌ ባንክም ማዕከሉን ጅግጅጋ ከተማ ላይ በማድረጉ በቀጣይ በተለያዩ አገራት ቅርንጫፎቹን በማስፋት ተጠቃሚ የሚሆንበት ዕድል አለው ብለዋል።

የሶማሌ ክልላዊ መንግስት ምክትል ፕሬዚዳንት ኢብራሂም ኡስማን ፋራህ በበኩላቸው፤ ሸበሌ ባንክ በሶማሌ ክልል እንደመቋቋሙ ከአካባቢው አገራት ጋር ያለውን ተመሳሳይ ባህልና ቋንቋ እንደመልካም ዕድል በመጠቀም የአገልግሎት አድማሱን በጎረቤት አገራት ማስፋት ይጠበቅበታል።

ባንኩ የአካባቢውን ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ትስስር በመጠቀም የፋይናንስ አቅሙን ለማጠናከር ከኢትዮጵያም አልፎ በተለያዩ አገራት መስራት ይኖርበታል ብለዋል።



የሶማሌ ክልልም የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ኢብራሂም ፤ ከወለድ ነፃ አገልግሎት ለሚሰጠው ሸበሌ ባንክ በቴክኖሎጂ፣ በሠው ኃይልና በተለያዩ ግብዓቶች እንዲጠናከር የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል።

አምባሳደር መሐሙድ ድሪር በበኩላቸው የቀጣናውን የፋይናስ ተደራሽነት ለማሳደግና የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን እንዲጎለብት ለማድረግ ከጉረቤት አገራት ጋር በትብብር መስራት ይገባል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ሸበሌ ባንክ ከአገር አልፎ በቀጣናው መስራት የሚችልበትን የገንዘብ፣ የዕውቀትና ሌሎች አቅሞቹን በማጠናከር በዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን ሰፊ ሥራ ይጠበቅበታል ብለዋል።

የሶማሌ ማይክሮ ፋይናንስ ወደ ሸበሌ ባንክነት ተቀይሯል፤ በዚህም ከወለድ ነፃ የሆነ አገልግሎቱን ለበርካቶች ማዳረስ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል ያሉት ደግሞ የባንኩ ፕሬዚዳንት ከድር አህመድ አብዲ ናቸው።

ባንኩ የብሔራዊ ባንክን መመሪያ በተከተለ አግባብ በኢትዮጵያ አዋሳኝ አካባቢዎች ለሚገኙ የኅብረተብ ክፍሎች ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ሸበሌ ባንክ ሸሪዓ ሕግን መሠረት በማድረግ ከ100 ሺህ በላይ ለሆኑ ሠዎች ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ማቅረቡን አስታውቋል።

የሸበሌ ባንክ አገልግሎት ማስጀመሪያ ሥነሥርዓት በተካሄደበት መድረክ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፣ የሶማሌ ክልል የኃይማኖት አባቶች እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎች ተገኝተዋል።

# ለቦንጋ ከተማ ልማት የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች እየተካሄዱ ነው

## - 190 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር ተሰብስቧል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የቦንጋ ከተማን መልሶ ለማልማት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ በክልሉ የሚገኙትን ሌሎች ከተሞችንም በጋራ ማልማት እንደሚቻል ማሳያ እንደሆነ የካፋ ዞን አስተዳደር አስታወቀ።

የካፋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ እንዳሻው ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የቦንጋ ከተማን መልሶ ለማልማት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ በክልሉ የሚገኙትን ሌሎች ከተሞችንም በጋራ ማልማት እንደሚቻል ማሳያ ነው። ከተማውን ለማልማት ሰፊ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ እንደሆነና፤ የማኅበረሰቡ ፍላጎት ሰፊ በመሆኑ ይህንንም በመንግሥት አቅም ብቻ ማሳካት ስለማይቻል ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች እየተካሄዱ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ለከተማው ልማት ከተማሪዎች ጀምሮ አርሶአደሮች፣ የዞኑ መንግሥት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎችና ባለሀብቶች እንዲሁም በሌላ አካባቢ የሚገኙ የዞኑ ተወላጆችም ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

ቦንጋ ከተማ አዲስ በተቋቋመው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የፖለቲካና የአስተዳደር ማዕከል በመሆኗ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ካቢኔያቸው እንዲሁም የክልሉ ተጠሪ ተቋማት ባለሙያዎች የአንድ ወር ደመወዛቸውን እንደለገሱ የገለፁት አቶ እንዳሻው። ይህ መሆኑ ክልሉን ለማልማት በጋራ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ መነቃቃትን እንደሚፈጥርና ቦንጋ ከተማን ማልማት ስንጀምር፤ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች ከተሞችንም የልማት ጥያቄያቸውን በጋራ መመለስ እንደምንችልና አብሮነታችንን በማጠናከር ማደግ እንደምንችል ማሳያ ነው ብለዋል።



አቶ እንዳሻው ከበደ

የካፋ ዞን መንግሥት ዋና ተጠሪና የቦንጋ ከተማ ልማት የገቢ አሰባሰብ አብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አስረስ አስፋው እንደገለፁት፤ ቦንጋ ከተማ ረጅም ዕድሜ ያላት ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የመጡ በርካታ ለውጦች ቢኖሩም አሁን ሌሎች አቻ ከተሞች የደረሱበት ደረጃ እንዳልደረሰችና ቀደም ባሉ ጊዜያት ዕድሜዋን የሚመጥን ስራ እንዳልተሰራ ገልፀው። ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ከተማዋ ያንን የሚሸከም አቅም ስለሌላት፤ ባሁኑ ወቅት ትኩረቱን በመሀል ከተማ ላይ ያደረገ ከተማዋን የሚመጥን አዲስ ፕላን ተዘጋጅቶ ገቢ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ አቶ አስረስ ተናግረዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት በዘርፉ ልምድ ያላቸው ሞያተኞች ቡድን ተዋቅሮ ጥናቶች እያካሄደ እንደነበር የገለፁት አቶ አስረስ፤ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ከተማዋን ለማልማት ከፍተኛ ዕድል አለ። ከዚህም



ውስጥ በበርካታ ወንዞች የተከበበችና የተለያዩ ለቱሪስት መዳረሻ የሚሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ መስህብ ያሉበት ስፍራዎች በዙሪያዋ እንደሚገኙ ታውቆ ከሕዝቡ ጋር፣ ከዞኑ አመራሮችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ተደርጐ የልማት እንቅስቃሴው እንደተጀመረ ነው ያብራሩት።

እንደ አቶ አስረስ ገለፃ፤ ከተማዋን ለማልማት በሚደረገው እንቅስቃሴ ከዞኑ ነዋሪዎች በተጨማሪ የቤንች ሸኮ ዞን 2 ሚሊዮን፣ የሸካ ዞን 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን፣ የኮንታ፣ የዳውሮና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች በየግላቸው አንድ አንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ እንዳደረጉ ጠቅሰዋል። በመጀመሪያ ዙር ለመሰብሰብ ከታቀደው 327 ሚሊዮን ብር ባጭር ጊዜ ውስጥ በድምሩ 189 ሚሊዮን 871 ሺህ ብር መሰብሰቡን ጠቁመዋል።

በከተማው ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ሁሉም ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው ያሉት አቶ አስረስ ፤ የልማት ስራዎችን በበላይነት የሚመራ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ይቋቋማል። ስራውንም በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ ለማጠናቀቅ እንደታሰበና በአጠቃላይ 550 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

# ጥናትና ምርምሮች ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተመራማሪዎች የተሻለ ጥናት እንዳይሠሩ አድርጓቸዋል

- ምሁራን

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚሰሩ ጥናቶች አብዛኛዎቹ ወደ ተግባር ባለመቀየራቸው ምርምር የሚሰሩ አካላት የተሻለ ጥናት እንዳይሠሩ አድርጓቸዋል ሲሉ ምሁራን ገለጹ፡፡

የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር መንግሥቱ ኡርጌሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጥናትና ምርምሮች የሚሰሩት ከፍተኛ የሆነ ሀብት፣ ንብረትና ዕውቀት ፈሶባቸው ነው፡፡

ሆኖም ጥናቶችን ተግባራዊ አድርጎ ኢኮኖሚውን መደገፍ ባለመቻሉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተጨማሪም ጥናትና ምርምሮችን በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ችግሮች መፍትሔ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ በስፋት አለመሰራቱ ተመራማሪዎች አዲስ የመፍትሔ ጥናት እንዳይሰሩ እያደረጋቸው ነው ብለዋል፡፡

ከለውጡ በኋላ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሰሩ ጥናቶችን ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ በተወሰነ መልኩ መሻሻል ማሳየቱንና ጥናቶችን የመጠቀም ፍላጎት ባለፉት አራት ዓመታት መጨመሩን ጠቁመው የታየው መሻሻል በቂ የሚባል እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

በአካዳሚክ ድህረ ምረቃ በተማሪዎች የሚሠሩ ጥናቶች የመመረቂያ ግብዓትን ለማሟላት የተሠሩ መሆናቸውና የጥናቶች መነሻ ሃሳብ በማህበረሰቡ መሰረታዊ ችግሮች ዙሪያ ባለመሠራታቸው ጥናቶችን ወደ ምድር አውርዶ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት አለመቻሉ እንደ ምክንያት አንስተውታል፡፡ ጥናትና ምርምሮች ሲሠሩ ማኅበረሰቡን ያሳተፉ፣ ተጠያቂነት ያለባቸውና ቀጥታ ችግሩን የተመለከቱ ችግር ፈቺ መሆን እንዳለባቸው ፕሮፌሰር መንግስቱ ገልጸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሯቸውን ምርምሮች በተወሰነ መጠን ተግባራዊ ማድረግ ቢችሉም ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያደርስ አካል ባለመኖሩ አብዛኞች የምርምር ውጤቶች በዩቨርሲቲዎች መደርደሪያ ላይ ተቀምጠው እንደሚገኙ የገለጹት ፕሮፌሰሩ የሀገሪቱ ሀብት፣ ንብረት፣ ጉልበትና ዕውቀት የፈሰሰባቸውን የምርምር ውጤቶች በመጠቀም ያሉትን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ተቋማት በትብብር መሥራት አለባቸው ሲሉ አመላክተዋል፡፡

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ዋና ዳሬክተር ፕሮፌሰር ታደሰ አወቀ እንደገለጹት፤ በተለያዩ መስኮች የተሠሩ በርካታ ጥናትና ምርምሮች ተግባራዊ ተደርገው የማኅበረሰቡን ችግሮች ከመፍታት ይልቅ ፋይዳ አልባ ሆነው እየባከኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በምርምር ማዕከላት የሚሠሩ ምርምሮችን እምብዛም ተግባራዊ እየተደረጉ አይደለም፡፡ ተማሪዎች ችግሮችን ለመፍታት ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን አፍስሰው የሚሠሯቸው ምርምሮች ተጠናቀው ውጤት ላይ ሲደርሱ ጥናቶችን ለመጠቀም የት ደረሱ ብሎ የሚጠይቅ አካል የለም ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ በሀገር በቀል ዕውቀት የተሠሩ ምርምሮችን ለመጠቀም መነሳሳቶች መታየታቸውን ፕሮፌሰሩ ገልጸው፤ የታየውን መነሳሳት ይበልጥ ለማጠናከር ተመራማሪው ምርምሩን የሚያቀርብበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ተመራማሪዎች ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ዕውቀታቸውን አፍስሰው የሠሩት የጥናትና ምርምር ሥራ ወደ መሬት ወርዶ የማኅበረሰቡን ችግር መፍታት አለመቻሉ ተመራማሪዎች የተሻለ ጥናት ለመሥራት ፍላጎት እንዳያድርባቸው ያደርጋል ብለዋል፡፡

እየባከነ የሚገኘውን ዕውቀት በመጠቀም የተሻለ ዕድገት ማስመዝገብና ችግሮችን በዕውቀት ላይ ተመረኩዞ መፍታት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

## ክልሉ በውሃ ፓምፖች

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሬት ወደ መስኖ ልማት ገብቷል። በገቡት የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በመጀመሪያ ዙር የመስኖ ስንዴ እየለማ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በሁለተኛው ዙር ደግሞ አትክልት እና ፍራፍሬን ለማልማት እቅድ ተይዞ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

በተለይ የመስኖ ስንዴ ምርት ልማት ላይ የተሳተፉ አርሶ አደሮች በከፍተኛ ቁጥር ተጠቃሚ ማድረጉን ገልጸው፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ አቅም ያላቸውን አርሶ አደሮች በማደራጀት እና አነስተኛ አቅም ያላቸውን አርሶ አደሮች ደግሞ በግል በመደገፍ ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰራው ስራ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ገልጸዋል።

ክልሉ ያለውን ከፍተኛ የውሃ አቅም በመጠቀም ከፍተኛ ምርት እንዲያመርትም አስችሏል ሲሉ አቶ ይበልጣል አክለዋል። በውሃ ፓምፖቹ በመታገዝ በሚሰራው የግብርና ስራ ላይ ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ተችሏልም ነው ያሉት።

በሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች የውሃ ፓምፖችን ማሰራጨት ተችሏል ያሉት ዳይሬክተሩ የውሃ ፓምፖች ፍላጎት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር በበቂ ሁኔታ ለማዳረስ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የውሃ ፓምፖቹ በድጋፍ እና በብድር እየቀረቡ መሆናቸው ለአርሶ አደሮች ከፍተኛ ጥቅም አለው፤ በመስኖ የማልማት ፍላጎትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ብለዋል።

የመለዋወጫ ችግሮችንም ክልሉ ባለው አቅም ለመፍታት እየሰራ መሆኑን እና የውሃ ፓምፖችን የጥገና ስራዎችን የሚሰሩ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ወደ ስራ ለማስገባት የተጀመሩ ጅምሮች መኖራቸውን የገለፁት አቶ ይበልጣል፤ ለውሃ ፓምፖቹ ግብዓት የሚሆን የነዳጅ አቅርቦት ችግር እንደሆነ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።



## በመዲናዋ በግማሽ ዓመቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲሰሩ የሚጠበቅ መሆኑንም አመላክተዋል።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት 89 ነጥብ አራት ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ የአስፋልት፣ የጠጠር፣ የእግረኛ መንገድ፣ የኮብልስቶን ንጣፍ፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ 50 ነጥብ ሁለት ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታ ሥራ ተከናውኗል።

በበጀት ዓመቱ 253 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታ፤ 611 ኪሎ ሜትር የመንገድ ጥገና ሥራዎች በአጠቃላይ 866 ኪሎ ሜትር በእቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን አስታውሰዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት 352 ኪሎ ሜትር ልዩ ልዩ መንገድ ጥገና ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዶም፤ 39 ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድ፤ እንዲሁም 18 ነጥብ ስድስት ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ ጥገና ማከናወን ተችሏል ብለዋል።

የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችን በተመለከተ በተለይ በክረምት ወራት በሚከሰት ጎርፍ ሳቢያ መንገዶች ለብልሽት እንዲዳረጉ ምክንያት መሆኑን በተደጋጋሚ መመልከት ተችሏል። ችግሩን ለመፍታትም በመጀመሪያው ስድስት ወር 263 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገዶች ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር የጥገና ሥራዎች መከናወኑን ገልጸዋል።

አቶ እያሱ እንደገለጹት በለቡ፣ በቦሌ ሚካኤልና ኢምፔሪያል አካባቢዎች በመገንባት ላይ ያሉት የተሸጋጋሪ ድልድይ፣ ትራፊክ ማሳለጫዎች ግንባታ ከ55 እስከ 65 በመቶ አፈጻጸም ላይ ናቸው።

ከፋይናንስ ጋር በተያያዘ በገጠመው ችግር እና በወሰን ማስከበር ምክንያቶች ለረጅም ጊዜ ሲጓተት የቆየው ከቃሊቲ ጉምሩክ ቱሉዲምቱ 11 ኪሎ ሜትር 50 ሜትር ስፋት ያለው የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት አሁን ላይ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር፣ የአፈር ቆረጣ ሥራዎች ተጠናቀው የሙሌት ስራ እየተከናወነ ነው።

አጠቃላይ የዚህ ፕሮጀክት አፈፃፀም 58 በመቶ ላይ የሚገኝና በከፍተኛ ፍጥነት እየተከናወነ ነው። በተያዘው በጀት ዓመት ለትራፊክ ክፍት ከሚሆኑት መንገዶች መካከል አንዱ መሆኑንም አመላክተዋል። ከኮዬፈጬ አደባባይ -ቃሊቲ- ቡልቡላ አደባባይም ጎንለጎን እየተከናወነ መሆኑንም ገልፀዋል።

በቀጣይ በበጀት ዓመቱ በእቅድ የተቀመጡ ልዩ ልዩ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች ለመፈጸምና የአፈጻጸም መዘግየት የታየባቸውን ፕሮጀክቶች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም በትኩረት የሚሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኮንትሮባንድን የመቆጣጠሩ ሥራ የላቀ ትጋትን ይጠይቃል!

የአገርን የምጣኔ ሀብት በመፈተን ከሚታወቁት መካከል አንዱ ኮንትሮባንድ ነው። በኮንትሮባንድ ንግድ የአገር ምጣኔ ሀብት በእጅጉ ይጎዳል፤ ህጋዊው ነጋዴ ከገበያ ለመውጣት ይገደዳል፤ የምርት ጥራት ጥያቄ ውስጥ ይገባል፤ በተለይም እንደ አደንዛዥ እጽና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶችና የታሸጉ ምግቦች በኮንትሮባንድ ወደ አገር እንዲገቡ ሲደረግ፣ ኮንትሮባንድ በአገር ምጣኔ ሀብት ላይ ከሚያደርሰው ችግር በተጨማሪ በሕዝብ ጤናና ሕይወትም ጠንቅ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ይህን የኮንትሮባንድ ንግድ አስከፊነት በሚገባ በመገንዘብ ለመቆጣጠር የተቀናጀ ጸረ ኮንትሮባንድ ተግባር ማከናወን ከጀመረች ቆይታለች። በዚህም በተለይ ከአገራዊው ለውጥ ወዲህ ውጤታማ ተግባሮች ተከናውነዋል። እንዲያም ሆኖ ግን የኮንትሮባንድ ንግድ የኢትዮጵያ ፈተና ሆኖ መቀጠሉን መረጃዎች እያመለከቱ ናቸው።

በተለያየ ጊዜ የወጡ የጉምሩክ ኮሚሽንና ቅርንጫፍ ተቋማቱን ዋቢ ያደረጉ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት፤ ብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የኮንትሮባንድ ሸቀጦች በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች፣ በተለያዩ አካባቢዎች ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ እንዲሁም ከአገር ሊወጡ ሲሉ ተይዘዋል። ጉምሩክ ኮሚሽንን ዋቢ ያደረገው ሰሞኑን የወጣው የኢፕድ ዘገባ እንዳመለከተውም፤ በአገሪቱ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ ቢጨምርም፣ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውም አገሪቱን ለከፍተኛ አደጋ በሚያጋልጥ ደረጃ እየጨመረ ነው።

ኮሚሽኑ እንደገለጸው፤ በአገሪቱ ከ2011 በጀት ዓመት አንስቶ የተከናወነው የጸረ ኮንትሮባንድ ንቅናቄ እየተጠናከረ ቢመጣም ችግሩም እንዲሁ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በ2011 በጀት አመት በሕገወጥ ንግድና በሕጋዊነት ሽፋን ሲንቀሳቀስ የነበረ የ9 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር፣ በ2012 በጀት አመት የ26 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ፣ በ2013 በጀት አመት 36 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ፣ በ2014 በጀት አመት የ50 ቢሊዮን ብር፣ እንዲሁም በተያዘው 2015 በጀት አመት የመጀመሪያ ግማሽ አመት ብቻ ደግሞ 40 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ኮንትሮባንድ መቆጣጠር ተችሏል።

ኮሚሽኑ እንዳለውም በርግጥም ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የተጠቀሱት የኮሚሽኑ መረጃዎች የሚያመለክቱትም፤ ከሚሽኑ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር ሰፊ ተግባር ማከናወኑን ነው። ኮሚሽኑ ለእዚህ ተግባር ሊመሰገን ይገባዋል።

ጉምሩክ ይህን የአገር ጠንቅ ለመቆጣጠር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ባከናወነው ተግባር በየአመቱ በብዙ ቢሊዮን ብር የሚገመቱ የኮንትሮባንድ ሸቀጦችን መያዝ ችሏል። ይሄ አንድ ስኬት ቢሆንም፣ ኮሚሽኑ ይህን ስኬት አስመዝግቤያለሁ ብሎም አልተኩራራም፤ ችግሩ እየሰፋ መምጣቱንም አስገንዝቧል። የኮንትሮባንድ ተግባሩ በየአመቱ በብዙ ቢሊዮን ብር እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ ሌላው የችግሩን አሳሳቢነት የሚያመለክት መረጃ ነው። ኮሚሽኑ በቁጥጥር ሥራው የያዛቸው የኮንትሮባንድ ሸቀጦች የተገመቱበት የገንዘብ መጠንም ችግሩ እጅግ ሰፊ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ይህን የኮንትሮባንድ ሸቀጥ መቆጣጠር ባይቻል ኖሮ የንግድ ሥርዓቱን በማዛባት፣ አገር በታክስና በመሳሰሉት ማግኘት ያለባትን በማሳጣት በምጣኔ ሀብት ላይ ምን ያህል ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ቁጥጥሩ ተጠናክሮ ቀጥሎም የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴው ለአገር ስጋት እየሆነ የሚገኘው። በየዓመቱ በብዙ ቢሊዮን ብር የተገመተ የኮንትሮባንድ ሸቀጥ እየተወረሰም ነው እንግዲህ የኮንትሮባንዱ እንቅስቃሴ የበለጠ ተጠናክሮ የቀጠለው። ችግሩ እየሰፋ መምጣቱ ሌላ የላቀ ሥራን የሚጠይቅ ተግባር ከአገሪቱ ፊት ለፊት መደቀኑን ያስገነዝባል።

ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር ጉምሩክን ጨምሮ የተለያዩ አካላት እንደሚሳተፉ ይታወቃል። በዚህ ላይ የኅብረተሰቡ ሚና አለ። አሁንም የእነዚህን አካላት ሚና ይበልጥ በማሳደግ መሥራት እንደሚያስፈልግ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት በሚገባ ይጠቁማል።

መንግሥት እንደ መንግሥት በጉምሩክ ከሚሽንና ሌሎች ባለድርሻ አካላቱ በኩል ሰፊ ሥራ እያከናወነ ይገኛል፤ ለዚህም የጸረ ኮንትሮባንድ ሥራው በከፍተኛ ሁኔታ እየተካሄደ ስለመሆኑና በቀጣይም በእዚህ ላይ ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት ያስገነዘበውን የኮሚሽኑን መረጃ በአብነት መውሰድ ይቻላል። በጸረ ኮንትሮባንድ ሥራው የሚሳተፉ አካላት ትብብርም ከመቼውም ጊዜ በላቀ መጎልበት ያለበት ስለመሆኑ መሬት ላይ ያለው እውነታ ያስገነዝባል።

ሕዝቡም ይህንን አገር ጎጂ የሆነ የኮንትሮባንድ ተግባር መዋጋት ላይ አተኩሮ መሥራቱን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የጉምሩክ ከሚሽንም ኅብረተሰቡ በጸረ ኮንትሮባንድ ሥራው እንዲሳተፍ ጥሪ ማቅረቡ የሕዝቡን ሚና ታሳቢ በማድረግ ነው።

ስለሆነም ኅብረተሰቡ ለኮንትሮባንዲስቶች ባለመተባበር፣ እንደተለመደው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱ ጥቆማዎችን በመስጠት፣ የኮንትሮባንድ ሸቀጦችንም ባለመጠቀም ይህን የአገርና የሕዝብ ጠንቅ የመዋጋት ኃላፊነቱን ላቅ ባለ የኃላፊነት መንፈስ መወጣት ይገባዋል።

ኮንትሮባንድ በሰፋና በከፋ ቁጥር የሚጠቀሙት ጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ብቻ ሲሆኑ የሚጎዱት ደግሞ አገርና ሕዝብ ናቸው። በኮንትሮባንድ ተግባር ውስጥ እጅግ ብዙ ቢሊዮን ብሮች እንደሚንቀሳቀሱ የጉምሩክ ኮሚሽን መረጃ ብቻውን በቂ ነው። ይህ ገንዘብና ሸቀጥ በሕጋዊ ገበያ ውስጥ ቢገባ አገር ልታገኝ የምትችለው ጥቅም ምን ያህል ትልቅ እንደሚሆን መገመት አይከብድም።

በአጠቃላይ ያሉት መረጃዎች ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር አሁንም የላቀና የተጠናከረ ሥራ ማከናወንን እንደሚጠይቅ ያመላክታሉ። ስለሆነም ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት አሁንም በላቀ ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሆነው ሆኗል፤ መጪውን ለማሳመር በቁርጠኝነት መሥራት ያስፈልጋል

ግርማ መንግሥቴ

ሰሞኑን ለጆሮ በቅተውና የውይይት አጀንዳ በመሆን አገር- ምድሩን ሞልተውት ከነበሩት ዜናዎች መካለከል አንዱ የ"3%" ጉዳይ ነው። ማለትም፣ "ከ980 ሺህ የ12 ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ተፈታኝ ተማሪዎች ውስጥ 50% እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች 28 ሺህ ወይም "3% ናቸው" የሚለው ነው።

ዜናው በዝርዝር እንዳስቀመጠው፣ "በማህበራዊ ሳይንስ ከታረመው ከ600 ውስጥ የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 524 ሲሆን፤ በተፈጥሮ ሳይንስ ደግሞ 666 ነው:: ይህንን ውጤት ተመርኩዘን ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስ ከ500 በላይ ያመጡት ተማሪዎች 10 ብቻ እንደሆኑ ማየት ተችሏል:: በተፈጥሮ ሳይንስ ደግሞ ከ600 በላይ ያመጡ ተማሪዎች 263 ናቸው።"

ውጤቱ እንኳን ባለቤቱን ሌላውንም ከው ያደርጋል። የየአገራቱ ትምህርት ሚኒስትሮችም "በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው በእኛም ላይ እንዳይደርስ" በሚል ርቆ አሳቢነት ተግባር ላይ እንዲጠመዱም ያደርጋል።

ጉዳዩን አስመልክተው ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ (የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር) ለመገናኛ ብዙኃን እንደተናገሩት ከሆነ፤ የፈተና ውጤቱ በየደረጃው ሁሉም የተፈተነበት ነው:: በተለይም መምህራንና ትምህርት ቤቶች በደንብ የማስተማራቸው አቅም የተፈተሸበት ነው::

ምክንያቱም በአስተማሩትና በአሳወቁት ልክ ተማሪዎቻቸው ውጤት አስመዝግበዋል:: ለምሳሌ፡ - በአጠቃላይ መደበኛ ተፈታኞች ትምህርት ቤቶች 2ሺህ 959 ሲሆኑ፤ ጥሩ ያስተማሩ ሰባት መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ አሳልፈዋል::

ከ50 በመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት የተመዘገበባቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ 1ሺህ 798 (60.76 በመቶ) ማምጣት ችለዋል:: የማስተማርና እውቀት የማስጨበጥ ችግር ያለባቸው 1ሺህ 161 (39.24 በመቶ)፣ ትምህርት ቤቶች ምንም ተማሪ ማሳለፍ አልቻሉም::

"የት ይደርሳል የተባለ ወይፈን ልኳንዳ ቤት ተገኘ" እንዲል ስነ-ቃላችን፣ የት ይደርሳሉ ያልናቸው ልጆቻችን የማይረባ ፖሊሲ ሰለባ ሆኑና እንዲህ ሆኑ። ይሁኑ እንጂ፣ ልጆቹ ገና ብዙ ዕድል ያላቸው ለግላጋ ወጣቶች እንደመሆናቸው መጠን ብዙም የሚያስጨንቅ ነገር የለባቸውም። ሁሉንም ነገር አሻሽለው የፈለጉበት ደረጃ የመድረስ ዕድል አላቸውና።

እርግጥ ነው፣ ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ "ሀገር አቀፍ ፈተናውን ከወሰዱት 896ሺህ 520 ተማሪዎች መካከል ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያመጡት 3 ነጥብ 3 በመቶ ብቻ ናቸው:: ማለትም ከተመዘገቡት 985ሺህ 354 ተማሪዎች መካከል 908ሺህ 256 ፈተና ላይ የተቀመጡ ሲሆኑ፤ በተለያዩ የደንብ ጥሰቶች በመቀጣታቸው የተነሳ 896ሺህ 520 ተማሪዎች ፈተናውን እንዲወስዱ ሆነዋል::

ፈተናውን ከወሰዱት ውስጥ 29ሺህ 909 ብቻ ናቸው ማለፍ የቻሉት::" በማለት የገለፁት ውጤት መንስኤው ማንም ሳይሆን የቀድሞው የትምህርት ፖሊሲ መሆኑን የሁላችንም ህሊና አሳምሮ ስለሚያውቀው አርቃቂዎቹን ሳንታዘባቸው ማለፍ ይከብደናል።

አፅዳቂዎቹን "ተሳስታችሁ ነበር። አልሰማ አላችሁ እንጂ መሳሳታችሁም ተነግሯችሁ ነበር። 'አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የምትሉት ነገር ትውልድ ገዳይ ነው' ተብላችሁም ነበር። በአጠቃላይ ከአርቃቂ አፅዳቂዎቹ በስተቀር ዜጋው በሙሉ 'እባካችሁ ...' ብሏችሁ ነበር።

ያገር ያለህ፣ የመንግሥት ያለህ . . . ያልተባለበት ምንም ዓይነት ጊዜ አልነበረም።" ሳንላቸው ብናልፍ ህሊናችን ይወቅሰናልና የወደፊቶቹ አርቃቂዎችም ሆኑ አፅዳቂዎች ከዚህ ሊማሩ እንደሚገባ አስምረንበት ማለፍ ግድ ይሆንብናል።

ይህ በወቅቱ አስተያየት ሰጪዎች "ትውልድ ገዳይ . . ." የተባለለት፤ እንዲሁም፣ በዘመነ ገነት ዘውዴ ከጣራ በላይ ሲፎከርለት የነበረ (ለእሳቸውም "ዮዲት ጉዲት" የሚል ስያሜን (በኤሊቱ አብዝቶ ይቀንቀን እንጂ ሕዝባዊ ተቃውሞ የወለደው ነው) ያጎናፀፈ የትምህርት ፖሊሲን ውድቀት፣ "ትሩፋቶቹ"ንና አስተማሪነቱን በዚህች ቅንጣቢ ገፅ ብዙ ማለት አይቻል ሆኖ እንጂ በትምህርት ፖሊሲያችን ላይ ቢነገሩ፤ ቢፃፉ ... የማያልቁ በርካታ ጉዳዮች አሉ።

ዋናው ነገር መማሩ ነውና፣ የአሁኑ "3% ብቻ . . ." መቼም፣ መቼም . . . እንዳይደገም ወገባችንን ታጥቀን ልንሠራ ይገባል። ክስተቱንም እንደ "መልካም አጋጣሚ" ልንወስደው ይገባል።

የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ "ልጆቹ አይደሉም የወደቁት። የወደቅነው እኛ ነን። እንደ አገር፣ እንደ መንግሥት . . . የወደቅነው እኛ ነን። ይህ የፈተና ውጤት አስተማሪ ነው:: ምክንያቱም ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም መምህራንና መንግሥት ያለባቸውን ክፍተቶች ለይተው ለቀጣይ እንዲሠሩ" ያደርጋቸዋል በማለት የተናገሩትም መልዕክቱ ይኼው እንጂ ሌላ አይደለም።

እኛም ይህንኑ እንጋራለን፤ ከደረሰው ኪሳራም ሁሉም ትምህርት ይወስዳል፤ ስህተቶችንም ያርማል ብለን እንጠብቃለን።

ይህንን ፈተና ከእስከ ዛሬዎቹ ለየት የሚያደርገው አንድ አቢይ ጉዳይ ቢኖር ተፈታኝ ተማሪዎቹ ከ50 በላይ በሚሆኑ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ገብተው ከፈተናው ከ – እስከ ድረስ እዚያው ቆይተው በጥብቅ ክትትል፣ ቁጥጥርና የፈተና ዲሲፕሊን ስር ሆነው የወሰዱት መሆኑ ነው።

ሂደቱም በአብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች ዘንድ ፈተናው ከአለፉት በተሻለ ሁኔታ ተፈታኞችን ማስተናገድ የተቻለበት፤ አንዳንድ ወላጆችን ያስደነገጠ ቢሆንም፣ አብዛኞቹን ደግሞ ጥሩ ተሠራ፤ እንዲያውም ለትምህርት ጥራቱ ሁነኛ መፍትሔ የሆነ፤ ኩረጃን እስከነ አካቴው ሊያስቀር የሚችል . . . አዲስ አሠራር ተብሎ የተመሰገነ ነው።

ሌሎች ተቋማትም "አይቻልም"ን ትተው፣ ልክ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ሁሉ፣ ያላቸውን ሪሶርስ በሙሉ ተጠቅመው ታላቅ ሞቢላይዜሽን በማድረግ ተአምር ይሠራሉ ብለን እንጠብቃለን። (ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ሞቢላይዜሽን ሲያደርግ ያቀናጃቸውን ተቋማት ልብ ማለት የሚያስፈልግ ሲሆን፤ ከመከላከያ ጀምሮ፣ አየር መንገድን አካትቶ፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ ትምህርት ቢሮዎችን፣ ወላጆችን ..... እኔ ሌሎች በርካቶችን እንዳሳተፈ ልብ በማለት ተሞክሮውን መውሰድ ያስፈልጋል።)

እንደ ማጠቃለያ፣ ሥራ ይሠራል። ስህተት ደግሞ መቼም ቢሆን ይኖራል። ትንሽ ከበድና ቸገር የሚለው ግን በትውልድ ላይ ሲሆን ነው። ያ ደግሞ ሆኗልና መጪውን ለማሳመር መጣር ያስፈልጋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ባለ በርኖስ መንዞች

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

በአልባሳት የሥነ-ጥበብ ታሪክ ውስጥ ኢትዮጵያውያን የሥልጣኔያቸውንና ማህበራዊ የእውቀት ደረጃቸውን ያሳዩባቸው የበርካታ እደ-ጥበብ ፈጠራ ባለቤቶች ናቸው። የቀድሞ እናት አባቶቻችን ምንም ዓይነት የቀለም ትምህርት ሳይቀስሙ ተፈጥሮ በሰጠቻቸው እውቀትና የሕይወት ልምድ ብቻ የራሳቸውን ፋሽን በራሳቸው የባህል ይዘት ለዘመናት ሲያበጁና ሲያጌጡ ቆይተዋል። እነዚህ ልዩ ልዩ አልባሳትም በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ይገኛሉ። ጥቂቶቹ ደግሞ በጭላጭል የመጥፋት ጎዳና በማዝገም ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል አንደኛው በርኖስ ነው። ለመሆኑ በርኖስ ምንድነው? ይህ ጥያቄ በአገራችን የሰሜን ሸዋ ክፍል ወደሚኖሩት የመንዞች መንደር ይወስደናል።

በርኖስ ማለት ከበግ ጸጉር ተሸልቶ የሚዘጋጅ በተለይ ድሮ ድሮ በሰሜን ሸዋ ደጋማ አካባቢዎች እና በተወሰኑ የጎጃም ክፍሎች የሚለበስ ወፍራምና ጥቁር ካባ መሳይ ልብስ ነው። በርኖስ ዝም ተብሎ ለብርድ ወይም ለፋሽን ያህል ብቻ የሚለበስ አይደለም። የራሱ የሆኑ የአለባበስ ሥርዓትና ጊዜ ያለው የክብር ልብስ ነው። ቀደም ሲል በነገሥታቱና በመኳንንቱ ዘንድ የሚዘወተር የጀግንነትና የልዩነት ማሳያ ነበር። ከዚያም ማኅበረሰቡ በደስታና ክብረበአላት ወቅት በክብር ይለበሳል። በደስታ ብቻም ሳይሆን በኀዘን ጊዜም ይጠቀሙት ነበር። የሚገርመው ነገር ደግሞ በርኖስ ለሁለት ተቃራኒ ማለትም ለደስታና ኀዘን እንዲያገለግል ተደርጎ በልዩ ዲዛይንና የፈጠራ ሃሳብ የሚሠራ መሆኑ ነው። ከትከሻ እስከ ጉልበት፣ ቁርጭምጭሚት የሚደርሰው ይህ በርኖስ ከላይ ወደታች፣ አሊያም ከተፈለገ ዘቅዝቆ መልበስ እንዲቻል ተደርጎ ነው የሚሠራው። አንድ በርኖስ ሁለት ዓይነት አለባበስና ሁለት ትርጉም አለው። ተዘቅዝቆ የሚለበሰው በኀዘን ወቅት ብቻ ነው። ሌላኛው ልዩ የዲዛይን ፈጠራ ደግሞ በበርኖሱ በአንደኛው የትከሻ ትይዩ በቀንድ ቅርጽ የተሠራ ወደላይ ሾጠጥ ያለ የጌጥ ክፍል መኖሩ ነው።



ይህ ቦታ ጠመንጃን ሸጎጥ አድርጎ ለመያዝ የሚያገለግል ምስጢራዊ ክፍል ነው። በዚህ መልኩ በርኖስን የሚለብሱ ሰዎች መሣሪያ ይያዙ አይያዙ ማንም ሰው አያውቅም። በተለያዩ ሙግቶችና በዳኝነት ሥርዓት ጊዜ በርኖስ የሚለበስ ሲሆን በዚህ ወቅት ሾጠጥ ያለው የጌጥ ክፍል በትከሻ ትይዩ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ይደረጋል። አንዳንዴም ከነጭ እጀ ጠባብ አቡጀዲ ጨርቅ እንዲሁም ከጠባብ ሱሪ እና ጭራ ጋር አብሮ የሚለበስበት ሥርዓት አለው፡፡

የበርኖስ አሠራር ከመጀመሪያው ጀምሮ ትልቅ እውቀትና ጥበብ ከጊዜ ጋር የሚጠይቅ በመሆኑ፣ በቀላሉ የሚሠራ አይደለም። የሚሠራው ከበግ ጸጉር ቢሆንም ነገር ግን የሁሉም በጎች ጸጉር አያገለግልም። ለዚህ የሚያገለግለው የጥቁር በግ ሪዝ ብቻ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም በርኖሱ ለስላሳና ለሰውነት ምቾትን የማይነሳ እንዲሆን ነው። እንደ አስፈላጊነቱ ግን የነጭ በግ ሪዝ ለማስጌጫነት መጠቀም ይቻላል። ለዚህ ሥራ የሚያስፈልገው የበግ ጸጉር የሚሰበሰበው በጎቹ በሕይወት እንዳሉ ጸጉራቸውን ብቻ በመሸለት ሲሆን እስከ አንድ አመት ድረስም በጎቹ መልሰው ጸጉሩን ያበቅላሉ። አንድ በርኖስ ሠርቶ ለማጠናቀቅ ሰባት ኪሎ ያህል የበግ ጸጉር ያስፈልጋል፤ ይህ ማለት ደግሞ ቢያንስ የሰላሳ በጎች ጸጉር ይፈተላል ማለት ነው።

በጎቹ ከተሸለቱ ወይም ጸጉራቸው ከተገፈፈ በኋላ በዚህ ጥበብ የተካኑት የመንዝ እናቶች የተሰበሰበውን የበግ ጸጉር ነጣጥለው በመበተን እንዲደርቅ ያደርጉታል። በእነርሱ የሙያ ቋንቋ ደግሞ 'ፍቶ' ያደርጉታል ማለት ነው። ከዚያም በደጋን እየነደፉ በማድበልበል አመልማሎ ይሠራሉ። የተድበለበለውንም ጸጉር በእንዝርት እያሾሩ ይፈትሉታል። በመቀጥልም በኋስ መልክ የፈተሉትን ፈትል እየተረተሩ የማድራት ሥራ ያከናውናሉ። እያንዳንዱን ሥራ በጥንቃቄ የከወኑት እናቶችም ከዚህ ደረጃ ላይ በማድረስ ቀጣዩን ሥራ ለሸማኔ ያስረክባሉ። የሸመና ሥራው ሲጠናቀቅም ወደ በርኖስነት ለመቀየር ጥቂት ሂደቶች የሚቀሩትን ይህንን አምሳለ በርኖስ ከንጹህ ውሃ ላይ ጋቢ እንደማጠብ በደንብ እየተረገጠ ሪዙ ጥቅጥቅ እንዲል ይደረጋል።

በዚህ ጊዜ ታዲያ ጥቁሩን ከጥቁሩ ጋር፣ ነጩንም ከነጩ ጋር ለይተን ካልረገጥነው በርኖሱ ወደ ነጭነት የሚቀየር በመሆኑ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። በስተመጨረሻም የባህልና ፋሽን ጠበብቶቹ ዲዛይነሮች በዚህ ሁሉ ሂደት አልፎ የመጣውን በርኖስ በማሳመር ወደ ልብስነት ይቀይሩታል።

በመንዞች ዘንድ በርኖስ የሚዘወተረው በወንዶች ሲሆን በተመሳሳይ የአሠራር ሂደት፣ በቀሚስ መልክ የሚዘጋጀው የሴቶቹ ልብስ ደግሞ መላወሻ ይባላል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ይህ ልብስ የመንዞች ዋነኛ የባህል መገለጫቸው ነበር። በጣም የሚወዱት የክብር ልብሳቸውም ጭምር የነበረ በመሆኑ በተለይ በገና በዓል የገና ጨዋታ ላይ የሚያጌጡት በዚሁ ልብስ ነው። በአሁኑ ወቅትም ይህ ባህል ሙሉ ለሙሉ ባይደበዝዝም እንደ ሻማ እየቀለጠ ሄዶ ለመጥፋት የቀረው ትንሽ ብልጭታ ብቻ ነው። የዚህ ጥበብ ባለቤቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየተመናመነ በጣት የሚቆጠሩ ያህል ብቻ ቀርተዋል። ታዲያ ይሄኛው ትውልድ ምን ይጠብቃል? ሙያዊ ጥበብ እንደ ወራጅ ወንዝ ነው፤ አንዴ ካለፈ ዳግም መልሰን አናገኘውም። አባቶቻችን ያለምንም ቴክኖሎጂ ከቆሙ በጎች ጸጉራቸውን ሸልተው በርኖስና ባና በሠሩበት አገር ውስጥ ቴክኖሎጂውን ታቅፈን ለቆዳና ሌዘር ምርቶች የምንጠቀመውን፣ የቆዳ ተረፈ ምርት የሆነውን የበጎችን ጸጉር የሚያህል ሀብት እንደዋዛ አውጥተን ስንጥል ቢያዩን ኖሮ እንዴት በሳቁብን ነበር።

እነዚያ ጥበበኛ አባቶቻችን፣ ያለንን ሀብት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ የምንኮራባቸው የራሳችን የሆኑ የፈጠራ ምርቶች ባለቤት መሆን የሚያስችሉንን በርካታ ጥበቦችን በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች አስቀምጠውልናል። እነዚህን ውብ የሆኑ የባህላዊ የፋሽን ፈጠራዎችን 'ሳይቃጠል በቅጠል' ብለን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ በባህላዊ የፋሽን አልባሳት ዘርፍ የሚሠሩ ተቋማትና ዲዛይነሮች ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ትልቅ የቤት ሥራ ነው።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## መቀመጥ .....

**ቦጋለ አበበ**

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እጅግ በጣም ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት መናገር ለቀባሪው ማርዳት ነው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጤናችንን ለመጠበቅ ከሚሰጠን ጥቅም በተጨማሪ ሥነልቦናዊ የሆኑ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ባለሙያዎች ደጋግመው ነግረውናል። ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ምክንያት የሆነኝን አንድ ጽሑፍ በጥቂቱ ልጥቀስ። ጽሑፉ ከአካል ብቃት እንቅስቃሴ አንጻር የሰው ልጆችን ዕድሜ በሁለት መክፈል ይቻላል ይላል። እነሱም ትክክለኛው ዕድሜ እና ፊዚዮሎጂካል ዕድሜ ናቸው።

ፊዚዮሎጂካል ዕድሜ የሚባለው ዕድሜያችን ስንትም ይሁን ስንት ሰውነታችን ላይ የሆነ ዕድሜ ክልል ላይ የሚገኝን ሰው የአካል ብቃት እንዲታይብን ያደርጋል ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ የ20 አመት ጎረምሳ ፊዚዮሎጂካል ዕድሜው 40 ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የአንድ የ60 አመት አዛውንት ፊዚዮሎጂካል ዕድሜ 40 ሊሆን ይችላል። የአንድ ሰው ፊዚዮሎጂካል ዕድሜ ከትክክለኛ ዕድሜው ከበለጠ ያሰው ያለ ዕድሜው እያረጀ ነው እንደማለት ነው። ፊዚዮሎጂካል ዕድሜን ትልቅ ወይም ትንሽ ከማድረግ አንጻር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከዚህ መገንዘብ የምንችለው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጤናን መጠበቅ ብቻም ሳይሆን ፊዚዮሎጂካል ዕድሜያችንን ዝቅ ማድረግ እንደምንችል ነው። ይህ ሁሉም ሰው የሚፈልገው ነገር መሆኑን እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል። ነገር ግን በተግባር ካልተደገፈ ፍላጎት ብቻ ዋጋ የለውም። እንደኛ ዓይነት ማህበረሰብ ደግሞ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ባህሉ የማድረግ ፍላጎቱ እንጂ ተግባሩ ላይ እንደሌለበት ግልጽ ነው። ፍላጎቱ እንዳለን የሚያሳይ አንድ ጥሩ አባባል አለ መቀመጥ.... የሚል። ግን ከአባባል አልፎ እንደ ጥሩ ባህል አዳብረነው አንገኝም።

የዛሬው ትዝብቴ ማጠንጠኛ ሃሳብም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። በኢትዮጵያ በተለይም በከተሞች በመንግሥትም ይሁን በግል የቢሮ ሥራ ላይ ተሰማርተን የምንገኝ በርካታ ዜጎች ጉዳይ ከአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ጥናት ቢደረግብን አሳሳቢ ደረጃ ላይ መገኘታችን አይቀርም። ያው የከተማ ኑሮ በብዙ ነገሮች የተወጠረና ብዙ የሚያሳስቡ ጉዳዮች ያሉበት እንደመሆኑ ብዙዎች ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ ትኩረት ባንሰጥ አይገርምም። ነገር ግን የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ጊዜና ትኩረት ሰጥቶ ማከናወን ባይቻል እንኳን ተመጣጣኝ ባይሆንም አማራጭ አለ። ይህ አማራጭ ቢያንስ በእግር መንቀሳቀስ የምንችልበትን ዕድል በአግባቡ መጠቀም ነው። ብዙዎቻችን ግን ይህን ዕድል እንደማንጠቀምበት የዕለት ከዕለት ውሏችንን መለስ ብለን እናስተውል።

> ከፈረንጆች ልንወስዳቸው ከሚገቡ ጥሩ ባህሎች ውስጥ አንዱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በየዕለቱ ማድረግን ነው

ብዙዎቻችን ጠዋት ተነስተን ወደ ሥራ ቦታ የምንሄደው በታክሲ ወይም በተለያየ የትራንስፖርት አማራጭ ነው። በርካቶቻችን ከሥራው ባህሪ ጋር በተያያዘ ሊሆን ይችላል ቢሮ ገብተን ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብለን ስንሠራ እንውላለን። ምናልባት ምሳ ሰዓት ላይ(የምሳ ዕቃ ካልቋጠርን) እዚያው በሥራችን አቅራቢያ ከቢሮ ወጣ ብለን እንመገባለን። በዚህች ጥቂት የምሳ ሰዓት ራቅ ወዳለ ቦታ በእግር ተጉዞ ለመመገብ የሥራው ባህሪና ያለችን ሰዓትም አትፈቅድልንም። ማታ ከሥራ መልስም ወደ እቤት ለመሄድ እዚያው በአቅራቢያችን የሚገኝ ትራንስፖርት ተጠቅመን ካልሆነ በእግር የተወሰነ መንገድ የመጓዝ ልምዱ የለንም። ቀጥሎም እቤት ገብተን በሥራ የደከመ አካላችንን አሳርፈን ለነገ ሥራ ራሳችንን ማዘጋጀት ነው። በነጋታውም የዕለት እንቅስቃሴያችን የተለየ አይደለም። ይህ ድግግሞሽ በብዙዎቻችን ዘንድ ቢያንስ በሳምንቱ የሥራ ቀናት ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል።

ቢሮ በሥራ ተጠምደው ቁጭ ብለው የሚውሉትን ለምሳሌ ያህል አነሳሁ እንጂ እንደ ማኅበረሰብም ለዚህ ችግር ተጋላጭ መሆናችን አከራካሪ አይደለም። በአሁኑ ወቅት በኅብረተሰቡ ዘንድ የጤና እና የአካል ብቃት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ልምድ እየተሻሻለ መምጣቱ ቢነገርም በጥናት ቢደገፍ ብዙ ርቀት እንዳልተጓዝን መታወቁ አይቀርም። ለዚህ አንዱ ማሳያ በኢትዮጵያ በየአመቱ ከሚሞተው ሰው 52 በመቶው ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት መሆኑን በቅርብ የተሠሩ ጥናቶችን መመልከት ይቻላል። ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሁሉ መንስኤያቸው እንቅስቃሴ ካለማድረግ ጋር ብቻ ባይያያዝም መቀነስ የሚቻለው በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ነው።

ከፈረንጆች ልንወስዳቸው ከሚገቡ ጥሩ ባህሎች ውስጥ አንዱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በየዕለቱ ማድረግን ነው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ ግዴታ ጂም መሄድ ወይም የተመቻቸ ነገር ማግኘት አይጠበቅብንም። ባለንበት ቦታ ሆነን በቀን የተወሰነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የማድረግ ባህሉ እና ቁርጠኝነቱ ቢኖረን ፈርጀ ብዙ የሆኑ ጥቅሞችን ማግኘት እንችላለን። ብዙዎቻችን ጋር ያለው እውነታ ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው። የነብር ከ50 ሳንቲም መንገድ እንኳን በእግራችን ለመሄድ የምንፈልግ ስንቶቻችን ነን? አንድ ኪሎ ሜትር የማይሞላ መንገድ በእግር ላለመጓዝ ታክሲ አንድ ሰዓት ተሰልፈን የምንጠብቅ ሰዎች ቁጥራችን ጥቂት አይደለም። ምናልባት አንድ ሰዓት ተሰልፈን በታክሲ ለመጓዝ የምንፈልገው መንገድ ቢበዛ በእግር ሰላሳ ደቂቃ ቢፈጅብን ነው። ይህንን መንገድ በእግር መጓዛችን ግን ጥቅሙ ሰዓት መቆጠባችን ብቻ ሳይሆን ከዚያም የዘለለ ነው። ሌላው ይቅርና ሙሉ ጤና ይዘን ሁለት ፎቅ በእግር ላለመውጣትና ላለመውረድ አካልጉዳተኞችና አቅመ ደካሞችን አሳንሰር (ሊፍት) የምንጋፋ ጥቂት አይደለንም።

በዚህ ረገድ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች እንቅስቃሴ የማድረግ ባህላችንን ለመቀየር በእረፍት ቀናት መንገዶች ከተሽከርካሪ ነፃ ሆነው ነዋሪዎች የእግር ጉዞና የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ የተጀመሩ ጥረቶች ወረት ሆነው መቅረት የለባቸውም። በብስክሌት የመንቀሳቀስን ጉዳይም መንግሥት ጀምሮት የነበረውን ሃሳብ ከግብ ሳያደርሰው ሊዘነጋው አይገባም።

# ነፃ ሃሳብ

## የአገር አቀፍ ፈተናው ውጤት ትዝብቶቼ

**ዳግም መርሻ**

ሰሞኑን የዘንድሮውን የ12ኛ ክፍል ፈተናን የወሰዱ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት የብዙዎችን ትኩረት ስቦ ነበር። ታዲያ ይህ ምን አዲስ ነገር አለው? ሊባል ይችላል። በርግጥም የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን ተፈታኝ ተማሪዎቹን አለፍ ሲልም ወላጅን ጨምሮ የቅርብ ቤተሰብ አባላትን ካልሆነ በስተቀር እንዲህ እንዳሁኑ የሕዝቡን ትኩረት በትልቁ ስቦ አያውቅም።

ጉዳዩ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሊሆን የቻለው ፈተናውን ከወሰዱት ተማሪዎች መካከል የማለፊያውን ነጥብ ማለትም ከ50 ፐርሰንት በላይ አምጥተው ያለፉት ተማሪዎች እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መሆኑ ነው። የተመዘገበው ውጤት ምን እንደሚነግረን ወደ መዘርዝር ከማለፋችን በፊት ስለ ትምህርት ምንነት (ፋይዳ) እንዲሁም ስለመጣንበት ሂደት በጨረፍታ ማየት ጥሩ ይመስለኛል።

የትምህርት ጉዳይ ለአገርም ለሕዝብም ትልቅና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በሌላ አነጋገር ትምህርት የአንድን አገር መፃኢ ዕድል ከሚወስኑት ጉዳዮች አንዱ ነው። ትምህርት የሰው ልጆችን ኑሮ ለማቅለል፣ የአገር ዕድገትና ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም ታሪክን፣ ባህልንና እውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል መሣሪያ ስለመሆኑ ብዙ ተብሎለታል።

የተለያዩ አካላት ትምህርት ዓለምን በመለወጥ ረገድ ያለውን ፋይዳ በተለያየ አጋጣሚ ሲናገሩ ይደመጣል። በሕዝቦችና በአገራት መካከል የስልጣኔ ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገውም እያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ አገር ለትምህርት በሚሰጠው ትኩረት፤ ትምህርትን ለማስፋፋትና በትምህርት ለማነፅ ባለው ቁርጠኝነት መሆኑን የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። ዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው የሚነገርላቸው የአገር መሪዎችም በተለያየ አጋጣሚ ለሕዝባቸው ንግግር ሲያደርጉ የትምህርትን አስፈላጊነት ሳይጠቅሱት አላለፉም።

ከዚህ አንጻር ቶሎ ብሎ ወደ አእምሮ የሚመጣው የዓለም ሕዝብ በነፃነት ታጋይነታቸው የሚያከብራቸው የሕንዳዊው ማህተመ ጋንዲ የማይዘነጋ ጥቅስ ነው። ማህተመ ጋንዲ «ፍፁም የሆነ ሰላም ለዓለም እንዲሆን የምንሻ ከሆነ ሕፃናትን በሚገባ በማስተማር መጀመር አለብን። » በሚል የትምህርትን አስፈላጊነት ተናግረዋል። በተመሳሳይ የነፃነት መሪውና የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላም «ትምህርት ዓለምን ለመቀየር ከሚያስችሉ መሣሪያዎች ሁሉ ከፍተኛ አቅም ያለው ነው። » በማለት ትምህርት ዓለምን ለመቀየር ምን ያህል አቅም እንዳለው ገልፀዋል።

ዓለምአቀፉ የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ትምህርት የሚለውን ቃል «የዕውቀት፣ ክህሎት፣ እሴቶች፣ አመለካከቶችና ልማዶች የምንጨብጥበት መንገድ ነው» ሲል ያስቀምጣል። በዚህ መሠረት ትምህርት ዜጎች በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብቁና በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ፣ ለሕግ ዘብ የቆሙ፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ የሆኑ በሚሉ ሀሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህ የሰው ልጅ ብቃቶች የሚገኙት በዘመናዊ ትምህርት ብቻ ነው።

የትምህርት ጉዳይ ሲነሳ አብሮ የሚነሳው ጉዳይ የትምህርት ጥራት ነው። ከዚህ አኳያ ትምህርት ተገቢና ተግባራዊ መንገዶችን ባሟላ ሁኔታ መሰጠት እንዳለበት ከማስገንዘቡ ጎን ለጎን የትምህርት ጥረትን ለማረጋገጥ የትምህርት ቤት መሠረተ ልማት፣ የትምህርት ግብዓት፣ የትምህርት መሣሪያ (ቁሳቁስ) መሟላት ወሳኝ መሆኑን ዩኔስኮ ይገልጻል።

የአንድ አገር ሁለንተናዊ እድገትና የሕዝቦቿ የኑሮ ደረጃ በሚኖራት የሰው ኃይል አቅም ይወሰናል። ዛሬ ላይ በሣይንስና ቴክኖሎጂ በልጽገው በአገራቸው ልማትን በማምጣት የሕዝባቸውን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ አገራት ልምድ የሚያሳይን ይህንኑ እውነታ ነው። ኃያላኑ እነ አሜሪካ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ካናዳ፣ በርካታ የስካንዲኔቪያን አገራት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም በቅርብ አመታት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ እመርታ በማምጣት የዓለምን ቀልብ እየገዙ ያሉት እንደ ደቡብ ኮሪያ፣ ቻይና፣ሲንጋፖር፣ ቬትናም፣ ማሌዢያ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት አገራት በአጭር ጊዜ ውስጥ አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ የደረሱት ለትምህርት በሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ነው።

በተቃራኒው ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት (በተለይም አብዛኞቹ ከሰሀራ በታች ያሉት) የትምህርት ስርጭትና ተደራሽነት፣ የአግባብነት እና የጥራት ጉደለት የመሳሰሉት ዋና ዋና ችግሮች ጎልቶ የሚታባቸው አገራት እንደሆኑ በስፋት ይነሳል። ይህ ደግሞ በልማትና የእድገት ጉዟቸው ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

ዘመናዊ ትምህርት በአገራችን ከተጀመረ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ዘርፍ ነው። ይሁን እንጂ ያለፉት መንግሥታት ይከተሉት በነበረው የተሳሳተ ፖሊሲ ሳቢያ አገሪቷ ላሉባት ውስብስብ ችግሮች ትርጉም ያለው ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማምጣት በቅቷል ለማለት አያስደፍርም። በተለይም የቀድሞው የኢህአዴግ አስተዳደር ለአገሪቱ ምሁራንና በአጠቃላይም ለትምህርት ጥራት ይሰጥ የነበረው ትኩረትና ግምት የወረደ የነበረ በመሆኑ አገሪቷ በብዙ ሁኔታ ትልቅ ዋጋ እንድትከፍል አድርጓታል።

ይህ ማለት ግን በደፈናው ትምህርት ለአገሪቷ ምንም ነገር አልፈየደም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ምንም እንኳን ሌሎች አገሮች በሄዱበት ፍጥነት እኩል ባንሄድም አገር በብዙ ሁኔታ ከትናንት ዛሬ የተሻለ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ መመስከር ይቻላል። ለዚህ ደግሞ የዘመናዊ ትምህርት ትሩፋትን የመቋደስ ዕድል ያገኙ ዜጎች ድርሻ የሚናቅ አይደለም።

ሆኖም መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር የትምህርት ሥርዓቱ ጠንካራ፣ በተግባር የተፈተሸ፣ በቂ እውቀትና ክህሎትን የተካነ ትውልድ ጥራትን ማዕከል ባደረገ አግባብ ከማፍራት ይልቅ ለሥርዓቶቹ እንዲመች ተደርጎ መለዋወጡና በየጊዜው የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንዲሆን መደረጉ ትውልድን በጥራት ከማፍራት አንጻር የሚፈለገውን ውጤት ሳያመጣ ቀርቷል።

በርግጥ ባለፉት አመታት የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በማስፋፋት የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት በማጎልበት በኩል በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከነብዙ ችግሮቹ በተለይ ባለፉት ሦስት አስርት አመታት በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች በየክልሉ መገንባታቸው ብዙ ዜጎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው እንዲማሩ ዕድል የፈጠረ በመሆኑ አገሪቷ ሰፊ የተማረ የሰው ኃይል እንዲኖራት አስችሏል።

ሆኖም ለትምህርት ተደራሽነት የተሰጠውን ትኩረት ያህል ለጥራቱ አለመሰጠቱ የትምህርቱ ዘርፍ ዋና ግቡን ሳያሳካ በውድቀት ጎዳና እንዲዳክር ተገዷል። ይህንን ተከትሎም በተለያየ ደረጃ በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ዜጎች የቁጥራቸውን መብዛት ያህል የሚጨብጡት የእውቀት መጠንና የክህሎት ደረጃ ጥያቄ ውስጥ የሚገባና አነጋጋሪ ሆኖ ቆይቷል።

ለአብነትም በቅርቡ ራይዝ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ በ168 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ በ9ሺህ ተማሪዎች ላይ ጥናት እንዳሳየው 68 በመቶ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች እና 51 በመቶ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ማንበብና መጻፍ እንደማይችሉ ያመላክታል።

በተመሳሳይም ትምህርት ሚኒስቴር በቅርቡ ባጠናው ጥናት መምህራን በሚያስተምሩበት የትምህርት ዘርፍ ተፈትነው 50 እና ከዚያ በላይ ያገኙት ከ30 በመቶ እንደማይበልጡ፣ 90 በመቶ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ያስቀመጠውን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት እንደማያሟሉ እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ከ1-4 ክፍል ያሉ ተማሪዎች ተምረው ሲጨርሱ ማንበብና ቁጥር ለመለየት እንደሚቸገሩ በግኝት መረጋገጡ የውድቀቱ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።

ከትምህርት ጥራት ችግር ጎን ለጎን ለትምህርት ሥርዓቱ እየተዳከመ መምጣት እንደምክንያት የሚወሰደው ፈተናዎቹ የፖለቲካና የብሔር መልክ እየተሰጣቸው የመምጣቱ ሁኔታ አንዱ ሲሆን ሌላው ከቅርብ አመታት ወዲህ በስፋት እየተስተዋለ የመጣው ኩረጃ፣ ስርቆት፣ ፈተናን በደቦ መሥራትና የተማሪዎች የሥነ ምግባር ችግር ነው።

በዚህም ምክንያት የፈተናው ሥርዓት በትምህርት ሚኒስቴር፣ በተማሪዎችና በወላጆች እምነት እንዳይጣልበት ከማድረጉም ባሻገር የመጪው ትውልድ ህልውና ላይ ስጋት ደቅኖ ቆይቷል። ሰሞኑን ከዚህ በፊት ከነበረው የተለመደው አሠራር ወጣ በማለት ተማሪዎች ለፈተና የተቀመጡበት የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት ይሄንኑ የትምህርት ዘርፍ ገመና ግልጥ አድርጎ አሳይቷል።

ትምህርት ሚኒስቴር ለሕዝብ ይፋ ባደረገው ስታትስቲክስ መሠረት ዘንድሮ የብሔራዊ መልቀቂያ ፈተናውን የወሰዱት ተማሪዎች ቁጥር 896 ሺህ 520 ያህል ሲሆን ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው ለመማር የሚያስችለውን ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት 3.3 ወይም 29,909 ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳው 7 ትምህርት ቤቶች ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች በሙሉ ያሳለፉ ሲሆን እነዚህም ትምህርት ቤቶች ደሴ ልዩ አዳሪ ት/ቤት፣ ኦዳ አዳሪ ልዩ ት/ቤት፣ ባህርዳር ስቴም ት/ቤት፣ ወላይታ ሊቃ ት/ቤት፤ የጎንደር ማህበረሰብ አቀፍ ት/ቤት እና ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ ለባዊ ት/ቤት መሆናቸው ተገልጿል።

በሌላ በኩል ተማሪዎቻቸውን ለፈተና ካስቀመጡ 2 ሺህ 959 የመደበኛ ትምህርት ቤቶች መካከል 1 ሺህ 161 የሚሆኑት ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ ማሳለፍ አልቻሉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ ትኩረት የሚስበው ጉዳይ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ውጤት ያላቸው ተማሪዎችም ውጤታቸው ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱ ነው።

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጤት ሃህዝ መሠረት አማካይ የተፈታኞች ውጤት በአማካይ 29.25 በመቶ ብቻ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው ኬሚስትሪ በአማካይ 33 በመቶ፣ እንዲሁም ዝቅተኛው ሂሳብ በአማካይ 25.5 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በሌላም በኩል በማኅበራዊ ሳይንስ ከ500 በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በመላ አገሪቱ አስር ብቻ ሲሆኑ፣ በተፈጥሮ ሳይንስ መስከ ከ500 በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ደግሞ በመላ አገሪቱ 263 ብቻ መሆናቸውን የወጣው መረጃው ያመለክታል።

ከዚህ በመነሳት የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎችና ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ዜጎች ውጤቱ ምን እንደሚያሳይና ምን አንደምታ እንዳለው ሲተነትኑና ሀሳብ ሲለዋወጡ ሰንብተዋል። በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ አብዛኞቹ ምሁራን ከሆነ ውጤቱ እንደ አገር የኢትዮጵያን የትምህርት ሥርዓት (ሲስተም) ምን ዓይነት ችግር ውስጥ እንዳለ በቂ ማሳያ ነው።

ለተማሪዎቻችን ውጤት ማነስ በርካታ ዝርዝር ምክንያቶችን መጥቀስ ቢቻልም በጥቅሉ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲጠራቀሙ የመጡት ብልሹ አሠራሮች ውጤት መሆኑ ይነሳል። በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የፖሊሲ ጥናት መምህር ከበደ ገነቴ (ዶ/ር) እንደሚሉት የተመዘገበው ውጤት ከትምህርት ግብአት እና ከመማር ማስተማር ሂደቱ ጋር ተያይዞ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የተለያዩ ችግሮች ተደማምረው የፈጠሩት ነው።

ለዚህም ከመምህራን እጥረት፣ ከመምህራን ብቃትና ተነሳሽነት፣ ከስልጠና ጉዳይ፣ ከተረጋጋ የመማር ማስተማር ሁኔታ፣ ከምዘናው ሥርዓት፣ ከትምህርት መሠረተ ልማት መሟላት፣ ከወላጆች ክትትል እንዲሁም ከተማሪው ተነሳሽነት (ቀናኢነት) ጋር የተያያዙ ክፍተቶችን እንደ ምሳሌ በማቅረብ ይሞግታሉ።

አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ደግሞ የውጤቱን ማነስ በአገሪቱ ከነበረው አለመረጋጋት፣ ተማሪውን የሚያዘናጉ ሁኔታዎች እየበረከቱ መምጣት እና አቋራጭ መንገድ ከመፈለግ ዝንባሌ ጋር ያያይዙታል።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሳሙኤል ክፍሌ(ዶ/ር) በጉዳዩ ዙሪያ ሲናገሩ «..የፈተናው ውጤት ስለ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ተማሪዎች ለትምህርት ስለሚሰጡት ትኩረት፣ ስለተማሪና መምህራን ግንኙነት፣ መምህራኖቻችንን ስላዘጋጀንበት፣ ስላሰማራንበት፣ ስላተጋንበት፣ ተጠያቂነትን ስላረጋገጥንበት፣ የትምህርት መዋቅሩ ለትምህርት ጥራት ያለበትን ኃላፊነት ምን ያህል እንደዘነጋ...ወዘተ አሳይቶናል፤» ሲሉ ይገልጻሉ።

ይሁንና በቀጣይ የትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጎ ከተሠራ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል አብዛኞቹ የልማት ማህበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ማህበረሰቡ ትኩረት ሰጥተው በከፈቷቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ዘንድሮ ካስመዘገቡት ውጤት እንደታየ ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር) ይገልጻሉ። ባንድ በኩል ውጤቱ አስደንጋጭ ቢሆንም በሌላ ጎኑ በቀጣይ ማን ምን መሥራት እንዳለበት እንዲሁም ችግሩ የት ጋር እንዳለ የሚጠቁም በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ያስረዳሉ።

አቶ ተፈራ ፈይሳ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ውጤቱ ምን አሳየን በሚለው ጉዳይ ላይ በሚኒስትር ዴኤታ ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር) በተነሳው ሀሳብ ይስማማሉ። እንደርሳቸው አገላለጽ የዘንድሮ በ 12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት የሚመለከተው የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ የተገነባበትን አግባብና ተማሪዎችን ከማብቃት አንጻር ያለበትን ግዙፍ ችግር ነው። ይሁንና ግኝቱ ቀጣዩን ትውልድ ኮትኩቶ ለማውጣትና ወደ ሚፈለገው መንገድ ለመዳዝ እንደማንቂያ ደውል የሚሆን ጥሩ ገጠመኝ ነው።

ትምህርት ሚኒስቴር የመጨረሻውን ርቀት ሄዶ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውን የፈተና ስርቆትና ኩረጃ እንዳይቀጥል ለማድረግ የወሰደው ቆራጥ እርምጃ ይበል የሚያሰኝና ለሌሎችም ተቋማት አርአያ የሚሆን ተግባር ነው። ይህ ጅማሮ ፈተናን በራስ ጥረትና ውጤት ብቻ ማለፍ የሚለው ሥነ ልቦና በተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በትምህርት አመራሮች፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ማስረጽ እስከሚቻልበት ጊዜ ድረስ ዘላቂ ሆኖ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ይህ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሥራ ነው።

በአጠቃላይ አመታትን ቆጥሮ ኩረጃን ባስቀረ ጥብቅ የፈተና አሰጣጥ ሂደት የተገለጠው የዘንድሮ የተማሪዎች ውጤት የሚነግረን ነገር ቢኖር የትምህርት ሥርዓቱ ትልቅ ስብራት ላይ ያለ መሆኑን ነው። ለዚህ ስብራት የፖለቲካ አመራሩ፣ ማኅበረሰቡ፣ ወላጅ፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የትምህርት አመራር...ወዘተ ሁሉም የተጠያቂነት ድርሻውን ይወስዳሉ የሚል እምነት አለኝ።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ለዚህ ዋናውን ኃላፊነት የሚወስደው መምህሩ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎቹን በእውቀት አንጾና በሥነ ምግባር ኮትኩቶ ለስኬት የሚበቃው መምህሩ ነውና። ተማሪው ብቃት የሚኖረው መምህሩ ብቃት ሲኖረው ነው። በመሆኑም ትውልዱን በተገቢው ሁኔታ በመቅረጽ የተሻለች አገር መፍጠር የሚያስችል የትምህርት ፖሊሲና የትምህርት ሥርዓት አገርን ከስብራት በሚያድን መንፈስ መተግበር ያስፈልጋል።

ከዚህ እኩል በትምህርት ትግበራው ውስጥ ተዋናይ የሆኑትን የመምህራንን አቅም ማሳደግ፣ ማብቃትና መደገፍ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የመማር ማስተማር ሂደቱን ምቹና ስኬታማ የሚያደርጉ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቃል። በዚህ አግባብ የመጣውን ውጤት መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀደም የነበረው የትምህርት ሥርዓት የፈጠረውን ህመም ምክያንቱን ከስር መሠረቱ (root cause) በዝርዝር በማጥናት መፍትሔው ላይ መወያየትና ችግሩን ዘላቂ በሆነ መልኩ ማከም ያስፈልጋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የአደጋ ተጋላጭነትን የሚቀንስ የአየር ጠባይ መረጃ ተደራሽነት

**ስምስም መንግሥቱ**

ይህ ወቅት መደበኛው የመኸር አዝመራ ስብሰባና በጥር ወር የተጀመረው የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እየተጠናቀቁ ያሉበትና በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ለበልግ ግብርና ዝግጅት የሚደረግበት ነው። በልግ አብቃይ አካባቢዎች ይህን ወቅት በእጅጉ ይፈልጉታል፤ በቀጣይ የሚጥለውን ዝናብ በመጠቀም የግብርና ሥራቸውን ለማካሄድ በቂ ዝግጅት ያደርጉበታልና።

የግብርናው ዘርፍ ባለድርሻ አካላትም አርሶ አደሩ ይህን ወቅት በሚገባ እንዲጠቀምበት ዝግጅት መረጃዎችን ግብአቶችን ያደርሳሉ። ሰሞኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ያወጣው መረጃም ይህንኑ ያመለክታል። ኢንስቲትዩቱ የየካቲት ወር በበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ለበልግ ሥራ እንቅስቃሴ ዝግጅት የሚጀመርበት መሆኑን ማስታወቁም ወቅቱ ለበልግ እርሻ ያለውን ፋይዳ ይጠቁማል።

ወቅቱ የበልግ ወቅቶች በሆኑት ከየካቲት እስከ ግንቦት እንዲሁም በበጋው ጥቅምትና ኅዳር ወራቶች መደበኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ሶማሌ ቦረና ጉጂ የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልል ቆላማ አካባቢዎች ወሳኝ ጊዜ እንደሆነም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚቲዎሮሊጂ ኢንስቲትዩት መረጃ ያመለክታል። ባለፈው አመት በዚህ ወቅት ይጠበቅ የነበረው ዝናብ ባለመጣሉ አካባቢዎቹ ለከፋ ድርቅ መጋለጣቸው ይታወሳል።

አካባቢዎቹ ዘንድሮም ለተመሳሳይ ችግር እንዳይጋለጡ በተለይም ወቅታዊ የአየር ጠባይ መረጃን ተደራሽ በማድረግ ችግሮችን ቀድሞ ለመከላከል እንዲሁም በክረምቱ ለሚከናወነው መደበኛ የግብርና ሥራ ወሳኝ የሆነውን የአየር ጠባይ መረጃ በወቅቱ ተደራሽ በማድረግ የተናበበ ሥራ መሥራት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ባለድርሻ አካላት፤ የአየር ጠባይ ትንበያ መረጃና ትንተና የሚሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚቲዮሮሎጂ ኢንስቲትዩት እጅና ጓንት ሆነው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲዩት የአየር ጠባይን በመተንተንና መረጃ በመስጠት ከግብርናው በተጨማሪ ለጤና፣ ለትምህርትና ለሌሎች ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ መረጃ በመስጠት ከአራት አስርት አመታት በላይ ዕድሜ አስቆጥሯል። ኢንስቲትዩቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ከመሆን፣ ከተአማኒነትና ከወቅታዊ ተደራሽነት ጋር ተያይዞ ይነሱበት የነበሩ አስተያየቶች አይዘነጉም። በቀደመው ጊዜ ግብርናውም ያን ያህል ለአየር ጠባይ መረጃ ትኩረት የሰጠ ነው ለማለት አያስደፍርም። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አሁን የምንገኝበት ዘመን ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕለት ተዕለት የሚሰጥ የአየር ጠባይ መረጃ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

መንግሥት በግብርናው ዘርፍ መጠነ ሰፊ እቅዶችን ይዞ እየሠራ ለመሆኑ እየታዩ ካሉ ውጤቶች መገንዘብ ይቻላል። ለዚህም በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በሌማት ቱሩፋት ልማት ሥራዎች ስኬት ለማስመዝገብ እያከናወነ ያለው ተግባር ይጠቀሳል። ክረምት ከበጋ ልማት እንዲከናወን በተቀመጠው አቅጣጫም የቆላ በጋ ስንዴ ልማት ለአብነት በማሳያነት ይነሳል።

የግብርና ሥራው በግብርና ሜካናይዜሽን እንዲታገዝም እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ የመንግሥትን ልዩ ትኩረት የሚያሳዩ ናቸው። የአየር ጠባይ ትንተናና መረጃውም ይህንን ሁሉ ጥረት በማገዝ ለስኬት እንዲበቃ በማድረግ ድርሻ አለው።



አቶ ፈጠነ ተሾመ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ እንደሚሉት፤ ኢንስቲትዩቱ በባለፉት ወቅቶች በሰጠው የአየር ጠባይ የትንተና መረጃ እና በመሬት ላይ ወይንም በተግባር የታየውን እንዲሁም በተለያዩ አስፈጻሚ ተቋማት ላይ ያመጣቸውን አሉታዊ እና አወንታዊ ተጽእኖዎች በመገምገም ለቀጣይ በልግ ወቅት የሚኖረውን የአየር ጠባይ በተመለከተ አስፈላጊውን ቅድመ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅቷል።

በዚሁ መሠረትም ያለፈው በጋ በአብዛኛው በሰሜን አጋማሽ የአገሪቱ ክፍሎች ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ የሚያይልበት፣ በደቡብ አጋማሽ የአገሪቱ ክፍሎችም በተለይ ሱማሌ፣ ቦረና ጉጂ ቆላማ ዞኖች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው እንደሆነና በነዚህ አካባቢዎች ከተሰጠ ትንበያ ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ተናግረዋል። ዋና ዳይሬክተሩ፤ ባለፉት ጊዜያት የተሰጡት ትንተናዎችና የነበራቸውን ጥንካሬዎች በመያዝ፣ ክፍተቶችንም በማረም ለቀጣዩ ዝግጅት መደረጉን ነው ያስረዱት።

በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ከሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች መካከል የደቡብ አጋማሽ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚገኙበት የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፣ አካባቢዎቹ በጋውም የክረምት ወቅታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። በተለይ በበጋ ወቅት ዝናብ የሚያገኙ የአገሪቱ አካባቢዎች ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ሶማሌ፣ ቦረና፣ ጉጂ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልል ቆላማ አካባቢዎች በተለይ ጥቅምትና ኅዳር ላይ ዝናብ የሚያገኙበት ወቅት እንደሆነ ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ አካባቢዎቹ በተጠቀሰው ወቅት ያገኙት ዝናብ ከመደበኛ በታች እንደሆነ በተሰጠው ትንበያ በግምገማ መለየቱን አመልክተዋል። በተለይም ቦረና፣ ጉጂ፣ የባሌ ቆላማ ዞኖች፣ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ሶማሌ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ሰገን ሕዝቦች አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የዝናብ እጥረት የተስተዋለባቸው እንደነበሩ አስታውሰዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሬ ማብራሪያ፤ የሚቲዎሮሎጂ ዝናብ ሰጪ ክስተቶች ግምገማ በሚደረግበት ወቅት በዋናነት በበልግ የኢትዮጵያን የአየር ጠባይ ወይንም የዝናብ ሁኔታን የሚወስነው የላሊና እና የኢሊኖ ሁኔታ እንዲሁም የውቂያኖሶች መሞቅና መቀዝቀዝ ነው። የባለፉት የበልግና የበጋ ወቅቶችም በላሊና ተጽእኖ ሥር የወደቁ ነበሩ። ክስተቱም የበልግና በጋ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር ችሏል። ላሊና በበልግና በበጋ ወቅቶች ከተከሰተ የዝናብ ሰጪ ክስተቶችን ያዳክማል። በተቃራኒው ደግሞ ላሊና በክረምት ወቅት ሲከሰት ጥሩ የዝናብ ወቅት ይሆናል።

በባለፈው በላሊና ተጽእኖ የተጎዱ የበልግና የበጋ ዝናብ ተጠቃሚዎች በዚህ የበልግ ወቅት ዝናብ የሚያገኙበት ሁኔታ ከተስፋ ያለፈ አይደለም። አሁን ባለው መረጃ ላሊና ተጽእኖ የሚያሳድርበት ሁኔታ እየቀነሰ በመሆኑ ነው ተስፋ …ደረገው። ወደ መደበኛ ዝናብ …ጣቱ ሁኔታ እስኪረጋገጥ …ረስ ግን የዝናብ እጥረት እንደማያጋጥም እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

ይህን መሠረት በማድረግም የበልግ ዝናብ ዘግይቶ እንደሚገባ፣ ላሊና ወደ መደበኛው ከመጣ ደግሞ ወደ መደበኛው የተጠጋ ዝናብ እንደሚኖር ነው የኢንስቲትዩቱ አጠቃላይ ትንበያ የሚያሳየው። ከአወጣጥ አንጻርም መደበኛውን የዝናብ ሂደት ተከትሎ እንደሚወጣም ትንበያው አካትቷል።

ይህን ተስፋ ሰጪ የሆነ ትንተናና የምክረ ሀሳብ መረጃ ወደ መልካም አጋጣሚ ቀይሮ መጠቀም ከግብርና፣ ከጤና፣ ከትምህርትና ከሌሎችም መረጃውን ከሚጠቀሙ ባለድርሻ አካላት እንደሚጠበቅ ዋና ዳይሬክተሩ አስገንዝበዋል። ኢንስቲትዩቱ በመካከል ላይ ያሉ ለውጦችን ተከታትሎ መረጃ የማድረስ ሚናው እንደተጠበቀ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋርም በተለያዩ የኮሚቴ አወቃቀሮች አማካኝነት የሚጠበቁ ሥራዎችን በመሥራት ለድርቅ አደጋ ተጋላጭነትን የመቀነስ ሥራ እንደሚሠራም አስታውቀዋል።

ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል ይነሱበት የነበሩ የመረጃ ተደራሽነትና የተአማኒነት ጉዳዮች እንዲሁም ግብርናን በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንደ አገር በትኩረት እየሠራ ነው። በተለይም በግብርናው ዘርፍ ወቅቱን የጠበቀ የአየር ጠባይ ትንተና መረጃ በማድረስ በመደገፍ በኩል ኢንስቲትዩቱ ያለውን ዝግጁነት የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ ኢንስቲትዩቱ ዋና ተልዕኮውን ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን በመጥቀስ ነው።

እሳቸው እንዳሉት፤ በተለይም በ2007 ዓ.ም ካጋጠመው የኢሊኖ ክስተት ጀምሮ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተካተቱበት ብሔራዊ የአደጋ መከላከል ኮሚቴ በማቋቋም በኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን መረጃ መሠረት በማድረግ ትንበያ የሚሰጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት ነው ሲሠራ የቆየው። የተቋቋመው ኮሚቴም በሚሰጠው ትንበያ የዝናብ እጥረት መኖሩን ከተገነዘበ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት ሰብአዊ ድጋፍ በሚመቻችበት፣ ችግሮችንም ለመቋቋም የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች በሚሠሩበት ሁኔታ ላይ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህ በተቀናጀ አሠራርም የእንስሳት መኖ እና ውሃ አቅርቦትና ሌሎችም የተከናወኑት ተያያዥ ጉዳዮች ሥራዎች መሠራታቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ይሰጥ የነበረው ትንበያም መሬት ላይ በተጨባጭ ከሚያጋጥም ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እንደነበር የኢንስቲትዩቱ የሥራ ግምገማ ያሳያል። የተሠራው ሥራ የጉዳት ተጋላጭነትን ባያስቀርም ለመቀነስ ግን አስችሏል።

ኢትዮጵያ በሁለቱም የአየር ሁኔታና ጠባይ ጽንፎች እንደሚያጋጥማት በምላሻቸው የጠቆሙት አቶ ፈጠነ፣ አንዴ ድርቅ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ክረምት ዋና የዝናብ ወቅታቸው በሆኑባቸው አካባቢዎች ላይ የጎርፍ ተጋላጭነት መኖሩንና ለዚህም ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይጠበቃል ብለዋል። እስካሁንም ሥራዎች ሲሠሩ የቆዩት በዚህ መንገድ መሆኑን ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ አመልክተዋል። የትንበያው ተአማኒነትም ከተሠሩት ሥራዎች ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ገልጸዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንጻር የሚገኝበትን ደረጃ አስመልክተው እንደገለጹት፤ ተቋሙ በደረጃ ነው ወደ ኢንስቲትዩት ያደገው። ይህም አንዱ የለውጥ እድገት ማሳያ ነው። በሌላ በኩልም በሰው መረጃን ከመሰብሰብ ጀምሮ በተራዘመ ጊዜ ወደ አውቶማቲክ የአየር መሰብሰቢያ መሳሪያ መሸጋገር የቻለው። ያደጉ አገራት የሚጠቀሙበት የአየር መሰብሰቢያ፣ በተለይም በከተሞች የአየር ብክለት መከታተያ ራዳር በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል። በሜትሮሎጂ አሰባሰብ ዙሪያ የነበሩ ክፍተቶችን በመሙላት በመረጃ አሰባሰብ ሌሎች አገሮች የደረሱበት ደረጃ በመድረስ ወቅቱ የሚጠይቀውን በጥራት የመረጃ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ኢንስቲትዩቱ ዝግጁ ሆኖ እየሠራ ይገኛል። ከባለድርሻ አካላት ጋርም የተናበበ ሥራ ለመሥራት የሚደረገው ጥረት ቀደም ሲል በተዘጋጀው ብሔራዊ የአየር ጠባይ ማዕቀፍ አገልግሎት በተከናወነው የሰነድ ስምምነት ፊርማ መሠረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

በአገሪቱ እየተከናወነ ባለው ልማት ላይ እስያገኘ ካለው ጠቀሜታ አንጻር ሲገመገም በተለይ ግብርናውን ጨምሮ ሁሉም የመረጃው ተጠቃሚ ባለድርሻ አካላት ጋር ብሔራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎት ማዕቀፍ ሰነድ በማዘጋጀትና ሰነዱም የጋራ እንዲሆን የተከናወነ ተግባር መኖሩንም ነው ያመለከቱት። በግብርናም በኩል የራሱ አግሮ ሚቲዮሮሎጂ በሚባለው ዘርፍ ላይ እስከ ልማት ጣቢያ ሠራተኛ ድረስ መረጃው እንዲደርስ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

አጠቃላይ ከአረንጓዴ አሻራ፣ እንዲሁም የሌማት ቱሩፋትን ጨምሮ እየተከናወነ ላለው የልማት ሥራ አጋዥ የሆነ መረጃ የመስጠት ሥራ እየተሠራ ነው የሚል እምነት በኢንስቲትዩቱ መኖሩን አቶ ፈጠነ አመልክተዋል።

‹‹የአገሪቱን የአየር ጠባይ በመረዳት ለዚያ የሚመጥን ስትራቴጂ በመንደፍ በተለይም በግድቦች ውሃ ይዞ የመጠቀም ጥረት ያስፈልጋል። ዝናብን በመጠበቅ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አይቻልም። በመሆኑም የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት አሟጦ ለመጠቀም ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል›› ሲሉም አስገነዘበዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በልግ በባህሪው ከፍተኛ የሆነ ሙቀት የሚስተዋልበት ሲሆን፣በክረምትና በበጋ ወቅቶች ከፍተኛ ቅዝቃዜ እንደሚስተዋለው በበልግ ወቅትም ሙቀት ማጋጠሙ የተለመደ ነው። ይህንን መቋቋም የሚያስችል በተለይም ከጤና አንጻር የተለያዩ ዝግጅቶች ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሲባል ግን አንድ ቀንም ቢሆን የጣለ ዝናብ መደበኛ የሚሆንበት ወይንም በበልግ ወቅት የጣለ ዝናብ ሆኖ ሊመዘገብ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ውጤትን የማከም ተግባር በዩኒቨርሲቲዎች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ባሳለፍነው ወር አጋማሽ የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ የፈተና ውጤት ይፋ መደረጉን ተከትሎ በርካታ ሀሳቦች ሲንሸራሸሩ ቆይተዋል።በተለይም ብዙዎችን ያስደነገጠና እንደአገር ወድቀናል ያስባለ እንደነበር ሁሉም ያስታውሰዋል።ማነው ተጠያቂው በሚልም ብዙ ሀሳቦች ተነስተው በየመድረኩ ውይይቶች ተደርጎባቸዋል።በዚህም የመፍትሄ ሀሳብ ናቸው ተብለው ከተጠቆሙት መካከል ለዛሬ ልናነሳው የወደድነው ሀሳብ አንዱ ነው።

ይህም የዩኒቨርሲቲዎች ማህበራዊ ተሳትፎ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚል ሲሆን፤ ምን ውጤት አመጣ።በተለይም በዘንድሮው ውጤት ላይ በሚል ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ካሳለፉ ሰባት ትምህርት ቤቶች መካከል ሁለቱን መርጠን አነጋግረናል።ትምህርት ቤቶችና የተደረገላቸውን የዩኒቨርሲቲዎች እገዛ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ይዘን ቀርበናል።

ተማሪዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ ካሳለፉ ሰባት ትምህርት ቤቶች መካከል የወላይታ ሊቃ አዳሪ ትምህርት ቤት አንዱ ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት በስፋት የሚታገዘው በወላይታ ልማት ማህበር ቢሆንም የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲም እንደ አንደኛው ካምፓሱ ስለሚቆጥረውም በሁሉም ነገር ያግዘዋል።ለአብነት በመምህራን ልማት ዙሪያ የትምህርት ዕድልን ከመስጠት ጀምሮ አጫጭር ስልጠናዎችን ወስደው ተማሪዎቻቸውን በእውቀት እንዲያጎለብቱ ይደግፋል።በተመሳሳይ ለሴቶችና ለወንዶችም የማደሪያና የመጸዳጃ ክፍሎችን በመሥራት ማስረከብ ችሏል።

ቤተ ሙከራና አይሲቲ ክፍሎችን የማደራጀት ሥራም የእሱ ሲሆን ወደሰባት የሚሆኑ የቴክኒካል ድሮይንግ መሣሪያዎችን ለትምህርት ቤቱ ከመስጠት ባለፈ ሊቃ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም ትምህርት ቤቶች በሳይንስ፣ ኢንጅነሪንግና ማትስ በስቲም ሴንተሩ ገብተው ተከታታይ ስልጠና እንዲወስዱም አድርጓል።

ዩኒቨርሲቲው ይህንን ሥራ ለመሥራት ያሰበበት ዋና አላማው የተሻለ ትውልድ፤ ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ማፍራት በመሆኑ ሲሆን የፈጠራ ሥራ ሠርተው እገዛ እንፈልጋለን ካሉ በራቸው ክፍት እንደሆነም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና የወላይታ ልማት ማህበር ቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር ታከለ ታደለ ይናገራሉ።

ዩኒቨርሲቲው አዳሪ ትምህርት ቤቱን የሚያግዘው በትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ውጪ ባሉ ለምሳሌ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የተዘጋጁትን ተማሪዎች የትምህርት መስኮችን እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው ግንዛቤ በማስጨበጥና በሌሎችም ተሳትፎን ያደርጋል።ዘንድሮም ወደ ዩኒቨርሲቲ ከሚገቡት ተማሪዎች ጋር ለመወያየት እቅድ ይዟል።

እንደአገር ማንኛውም ነገር መመራት ያለበት በእውቀት ነው የሚሉት ፕሬዚዳንቱ እውቀት ያልታከለበት ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካም ሆነ ማህበራዊ መስክ ከግብ ሊደርስ አይችልም።ስለሆነም የእውቀት ምንጭ የሆኑ ትምህርት ቤቶች በአግባቡ መገንባትና ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት አለባቸው።ለዚህ ደግሞ በየደረጃው መሥራትና ሁሉም የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል፡፡

በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው።በዚህም እንደ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢያችን ካሉ ትምህርት ቤቶች 30 የሚሆኑትን በመውሰድ መደገፍ አለብን ብለን እየተንቀሳቀስን ነው የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዩኒቨርሲቲው መንግሥት የማይደርስባቸው አካባቢዎች ላይ ጭምር በመውረድ ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት ባሻገር በግብዓት የመደገፍ ሥራ እያከነ እንደሆነ ያነሳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ድጋፍና ክትትል ዝም ብሎ በራስ ፈቃድ የተከወነ አይደለም።በሕግና በመመሪያ ጭምር የተቀመጠ ነው።ለዚህም ማሳያው ዩኒቨርሲቲዎች ሲመሠረቱ ሦስት ሥራ ተሰጥቷቸው መሆኑ ነው።የመጀመሪያው መማር ማስተማር ሥራው ነው፤ ሁለተኛ ጥናትና ምርምር ማድረግ ሲሆን፤ ሦስተኛው ደግሞ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ነው።ከሁሉም በላይ ደግሞ ሦስተኛው ውስጥ የሚካተት በአዋጅ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል።ይህም በከፍተኛ ትምህርት



ፕ/ር ታከለ ታደሰ



አቶ አቤል ጫላ

አዋጅ 11/52/ 2011ዓ.ም ላይ እንደሰፈረው ዩኒቨርሲቲዎች በአካባቢያቸው ያሉትን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአደረጃጀት፣ በአሠራር፣ በአመራር፣ በግብዓት፣ በክትትልና ድጋፍ ማገዝ አለባቸው ይላል።ይህንን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ዩኒቨርሲቲዎቻችን ምን ያህል እየሠሩ ነው ከተባለ ሁሉም በራሱ የሚመልሰው ይሆናል።

እንደ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ግን በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነ የሚያነሱት ፕሮፌሰር ታከለ፤ ትምህርት ቤቶችንም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በግንባታ፣ በመሠረተ ልማት ማሟላት ለመማር ማስተማሩ የሚያግዙ ግብዓቶችን በመደገፍ እገዛን ይደርጋል።ለምሳሌ፡- ብዙዎቹ ትምህርት ቤቶች የውሃ ችግር ያጋጥማቸዋል።ዩኒቨርሲቲው ደግሞ ውሃ የሚያገኙበትን መንገድ በመፍጠር፤ መንገድ ያስቸገራቸውንም እንዲሁ መንገዶችን በመሥራት፣ መጸዳጃ ቤቶችን ሠርቶ በማስረከብ፣ የትምህርትና የማደሪያ ክፍሎችን ጭምር ገንብቶ በመስጠት ድጋፎች ተደርገዋል።

በቅርቡ ብቻ ዩኒቨርሲቲው 20 ሚሊዮን ብር በመመደብ ድቡላ ፋንጎ አካባቢ አንድ አዳሪ ትምህርት ቤት እየተገነባ ሲሆን፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ 1ሺ 500 ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ተቀብሎ ያስተናግዳል።መንግሥት ባወጣው የትምህርት ቤት አሠራር መስፈርት መሠረት ሁሉንም ነገር ያካተተ ይሆናል።በሚቀጥለው ዓመት ለትምህርት ዝግጁ እንዲሆንም ከአሁኑ በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው።የትምህርት ግብዓቶችን ሳይቀር ለማስገባት ከኢትዮጵያ ትምህርት መሣሪያዎች ማደራጃ ጋር በመነጋገር የግዢ ሥራ ሂደቱ እየተከናወነ ነው።

ትምህርት ቤቱ ሙሉ ወጪው ብቻ ሳይሆን የአስተዳደሩ ሥራ ጭምር የሚመራው በዩኒቨርሲቲው ሲሆን፤ «ከኬጂ ወደ ፒኤችዲ» የሚል መርህ በመያዝ ለመሥራት የታሰበበት ነው።በተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲው ከወላይታ 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የነበረው ትምህርት ቤት በአውሮፕላን ማረፊያ መሠራት ምክንያት ተማሪዎች በቀላሉ ሳይረበሹ ለመማር ይቸገራሉ።ስለሆነም ይህ እንዳያጋጥማቸው በማሰብ ትምህርት ቤቱን በማንሳት ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድ 25 ሚሊዮን ብር በመመደብ ለመስራት ወስኗል።አሁን በርካታ ተግባራትን እያከናወነም ይገኛል።ይህንን የማያደርግ ከሆነ ግን ስለ ትምህርት ጥራት፣ ስለ ትምህርት አግባብነት፣ ስለትምህርት ፍታዊነትና ተደራሽነት ማንሳት አይችልም።እናም የራሳችንን ድርሻ እየተወጣን ከሄድን ተጠያቂነትን ከራሳችን እያወረድን እንሄዳለን ብሎ ያምናልና ተግባሩን እየከወነ ነው ይላሉ ፕሮፌሰሩ።

እንደአገር የወደቅንበትን የትምህርት ዘርፍ እንደአገር ለመገንባት ዩኒቨርሲቲዎች ያላቸው አቅም ትልቅ ነው።ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲዎች እውቀትም፣ ቴክኖሎጂም፤ ገንዘብም አላቸው።በአግባቡ መጠቀም የሚችሉትም እንዲህ ዓይነት ተግባራትን መከወን ሲችሉ ነው።ኅብረተሰቡን ይዘው አገርን ማሻገር ይችላሉ።ለችግሮች መፍትሄም ይሰጣሉ።ስለሆነም ቆራጥ ሆነው በተሰጣቸው ልክ መሥራት አለባቸው።

እንደአገር የወደቅነውና ያመጣነው ውጤት መታከም ስላለበት መንግሥት በዚህ ሁኔታ አይቀጥልም።እንደአዲስ ፖሊሲና አቅጣጫ ያስቀምጣል።ለዚህ ደግሞ ሁሉም ጋር የሚደርስ ሥራ አለ።እናም ዩኒቨርሲቲዎች ከአሁኑ ቢላመዱትና ወደ ሥራ ቢገቡ ጊዜን መጠቀም እንደሚችሉም ያብራራሉ።ዩኒቨርሲቲው ለወላይታ ዞን በመምህራን ልማት ከ400 በላይ መምህራን ማሰልጠን መቻሉን፤ በዞኑ በነፃ የትምህርት ዕድል (ስኮላር ሺፕ)ም ከ 2ሺ በላይ ሰው ሙሉ ወጪያቸውን ሸፍኖ እያስተማረ እንደሚገኝም ያነሳሉ።

ይህ ዕድል በተለይ የሚያግዘው አቅሙም አማራጩም ለሌላቸው ራቅ ካለ የገጠር ክፍል ለሚመጡ ተማሪዎች ነው።በተለይም ራዕይን የሰነቁ ጎበዝ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ማግኘት ለማይችሉት ተስፋ ይሰጣል።በተመሳሳይ ትምህርት የማግኘት አማራጫቸው እጅግ ዝቅተኛ ለሆኑ ለአካል ጉዳተኞችና ለሴቶችም ጥቅሙ ቀላል አይደለም።ችሎታው ቢኖራቸውም አጋጣሚዎች ስለማይፈቅድላቸው ቤታቸው ተሸሽገው ይቀራሉ።እናም እነርሱ እንዲወጡና ለአገር ማበርከት ያለባቸውን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል።

ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶች እንደ አገር ያሉበት ሁኔታ ቅርብ አይደለም።ቅርብ ያሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በብዙ አቅም የተደራጁ እንዳልሆኑ ሁሉም ያውቀዋል።እናም ዩኒቨርሲቲዎች እዚህ ላይ መሥራት ተማሪዎችን በብዙ መልኩ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።አገርም ብትሆን ከውድቀት እንድትላቀቅ ያግዛታል።የተሻለ ተማሪን በማፍራት ሁነኛ መፍትሄ ያመነጫልም።በተለይም ጎበዞቹን አውጥቶ ለአገር ጠቃሚ ማድረግ ላይ ያለው ፋይዳ ቀላል አይሆንም።

ሴቶች በቤተሰብ ጫና፣ በትምህርት ቤቱ ርቀትና በጾታዊ ጥቃት ምክንያት ከትምህርታቸው እንዳያቋርጡ የሚያደርግም ነው።በውጤታቸው ላይም ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ያግዛል።ከሁሉም በላይ አሁን ያየነውን ውጤት ላለመድገም ያስችለናል።መንግሥት የያዘውን 25 በመቶ የማድረስ እቅድም ለማሳካት ሁነኛ መፍትሄ ነው።

መንግሥት ወደ 2ሺ የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት እቅድ ይዟል።በዞን ደረጃ ከልማት ማህበሩ ጋር በመሆን እስከ ስድስት አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታስቧል።ዩኒቨርሲቲው ደግሞ በራሱ የጀመረው አንድ አዳሪ ትምህርት ቤት አለ።በቀጣይ ዓመትም ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ እየተሠራ ነው።ነገር ግን ሁሉንም በእኩል የጋራ ነገር ያስፈልጋል።በተለይም በክልልና ዞን አካባቢዎች ላይ።የጋራ ነገር ከሌለ ምንም ነገር ስኬታማ አይሆንም።እናም እንደመንግሥት ይህንን ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ጠንከር ያለ ህግ ቢወጣ መልካም ነው ይላሉ ፕሬዚዳንቱ ፕሮፌሰር ታከለ።

የዩኒቨርሲቲዎች በዘርፉ ላይ ድርሻ ኖሯቸው ታችኛው ክፍል ላይ ወርደው መሥራታቸው ጠቀሜታው ከግለሰብ አልፎ አገር ላይ የሚያርፍ ነው የሚሉት ደግሞ በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ ፕሪኒስፓል አቶ አቤል ጫላ ናቸው።እርሳቸው እንደሚሉት፤ የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስን ይዞ በመሥራት ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎችን እንደአገር ማፍራት የቻለ ተቋም ነው።ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የሚለየው ይህ ባህሪው ይመስለኛል።ሌሎቹ የመምህራን ልማት ላይ፣ ታችኛው ክፍል ወርደው በተለያየ መንገድ የሚደግፉበት ሁኔታ ይኖራል።አንድ ካምፓስ ፈጥረው የሠሩ ግን ያሉ አይመስለኝም።ስለዚህም ቢያሰፉትና ቢሠሩበት ብዙ ጥቅም ያስገኛል።

ይህ ትምህርት ቤት ሲጀመር እንደፕሮጀክት ብቃት ያላቸውን የተለያዩ ተማሪዎች ሰብስቦ ለማስተማር ነበር።ነገር ግን ከሁለት ዓመት ላይ መቀጠል አልቻለም።ስለዚህም ተማሪዎቹ መበተን እንዳለባቸው ሲታመን ይህ ያሳሰበው የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሁለት ዓመት ተምረው የአስረኛ ክፍል አገራዊ ፈተና ተፈትነው መበተን የለባቸውም በማለት ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመነጋገር ከአለው በጀት ላይ ቀንሶ ትምህርቱን አስቀጥሎታል።

እነርሱን መደገፍ አገርን ከፍ ማድረግ እንደሆነ ዩኒቨርሲቲው ያምናል የሚሉት አቶ አቤል፤ ከተለያየ ርቀት ላይ የሚመጡ ተማሪዎች በአቅራቢያቸው ሆነው የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ፣ ከበጀት አንፃርም መጋራትና የተሰጠውን ለሚፈለገው አላማ ለማዋል ይጠቅማል።በተጨማሪም መምህራን ለአገራቸው የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ያሰፋዋል።ምክንያቱም ታች ድረስ ወርደው እንዲያስተምሩ ይሆናሉና የእኔነት ስሜትን ይፈጥራል።መጠቋቆምን ያስቀራል።ትውልድ ቀረጻ ላይም ትልቅ አቅም ይፈጠራል።

የትምህርት ቤቱን ሙሉ ወጪ የሚሸፍነው ራሱ ነው።በዚያ ላይ በዩኒቨርሲቲ መምህራን መስፈርት መምህራንን አወዳድሮ ቀጥሮ ያሠራል።ይህ ሲባል ግን አጋዥ የለውም ማለት አይደለም።ምክንያቱም ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እና ከአራዳ ክፍለ ከተማ ጋር በመመካከር የተለያዩ ሥራዎች ላይ በጋራ ይተባበራል።ለአብነት የአራዳ ክፍለከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት የቀዳማዊ ምኒልክ ትምህርትቤትን ሊሰጠው ችሏል።በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስቴር ከሌሎች መደበኛ ትምህርት ቤቶች ይልቅ የሚደገፍበትን ሁኔታ አመቻችቶ ያውቃል ይላሉ አቶ አቤል።

እንደኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሁሉ እነዚህ አዲስ አበባ ላይ ከፍተኛ አቅም ያላቸውና ብዙዎችን መደገፍ የሚችሉ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርቱ ዘርፍ ላይ የተወሰነ አቅማቸውን እንኳን ተጠቅመው ድጋፍና ተሳትፎ ማድረግ ቢችሉ በዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ይህንን ያህል በማድረጉ ብዙዎችን ከዘንድሮው ማዕበል መታደግ ችሏል።በተጨማሪም ለቀጣይ አገር ጠቃሚ የሆኑ በእውቀትም በስነምግባርም የተሻሉ ትውልዶችን አፍርቷል።ስለሆነም የእርሱን ፈለግ ቢከተሉና አገርን በዘርፉ የሚታደጉ ዜጎችን ቢፈጥሩ መልካም ነው ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉም።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 6ኪሎ ካምፓስ፣ አራትኪሎና አምስት ኪሎ ካምፓሶች አለፍ ሲል ደግሞ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ካምፓሶች በትምህርት ዘርፍ ትልልቅ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ናቸው።ሆኖም አልሠሩበትም።ስለዚህም እነርሱም የሚሳተፉበትን ምህዳር ቢያሰፉ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ብዙ ፈጣሪና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ልጆችን ማፍራት ይቻላል ይላሉ።

ዩኒቨርሲቲዎች የሚያግዟቸው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው በርካታ ጠቀሜታዎች አለው ለአብነት መምህራን በተሻለ አቅም ሰልጥነው እንዲወጡ ያግዛል፤ ተወዳዳሪ እንዲሆኑም ያስችላል።በተመሳሳይ የትምህርት ዕድሎችን እንዲያገኙም ዕድል ይፈጥራል።ከሁሉም በላይ ደግሞ በትምህርት መስካቸው የተሻለ አቅም ኖሯቸው የተሻለ ተማሪ እንዲያፈሩ ይሆናሉ።በተመረጠ መምህር፣ በተመረጠና በተሻለ የመማር ማስተማር ሥራ የታገዘ ተማሪ ደግሞ አገር ወዳድ ብቻ ሳይሆን ለአገር የሚሠራ መሆኑ አይቀርም።ስለዚህም እንደአገር የወደቅንበት ሁኔታ በቀላሉ መታከም ይቻልም ባይ ናቸው።እኛም ህመሙን ያወቀ መድኃኒት ለማግኘት የሚሳነው ነገር የለምና በአዋጅ የተሰጠን ኃላፊነት መወጣት ይገባል በማለት ለዛሬ አበቃን፡፡

# ‹‹ኢትዮጵያ ብዙ ውሃ ማልማት የሚያስፈልጋት የውሃ እጥረት ውስጥ ያለች አገር ናት››

**ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ**
**የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር**

አስቴር ኤልያስ

**የውሃ መገኛ ቦታው የተለያየ ነው፡፡ በከርሰ ምድርም ሆነ በገጸ ምድር ያለውን ውሃ አገራት እንደየፍላጎታቸውና እንደማልማት አቅማቸው ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ እንደዛ በማድረግም የዜጎቻቸውን የንጹህ መጠጥ ውሃና የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት በብርቱ ሲታትሩ ይታያሉ፡፡ ኢትዮጵያ ምንም እንኳ ያላትን ውሃ አሟጥጣ ለመጠቀም የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር ማነስና የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት ቢይዛትም፤ ያላትን ውሃ ባላት አቅም ለመጠቀም በመጣር ላይ ትገኛለች፡፡ በእርግጥ ከውሃ ሀብት ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ኢትዮጵያውያኑም ሆኑ ሌሎች ጎረቤት አገራት ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ነች›› የሚለውን ትርክት እውነት አድርገው ሲጠቅሱ ኖረዋል፡፡ ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነና ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት በምን አግባብ እየተጠቀመች እንዳለ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ ጋር አዲስ ዘመን ያደረገውን ቆይታ አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡**


ፎቶ፡-አዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት ይባላል፤ ይህ ምን ማለት ነው?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** ይህ ጥያቄ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛ የመጣ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ይህ ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ነች›› የሚለው አባባል በብዛት ሲገለጽ ቆይቷል፡፡ አባባሉም ትክክል ተደርጎ ተቀባይነትን አግኝቶ ቆይቷል፡፡ እንዲያም ሆኖ ጥያቄው መነሳቱ አግባብነት ያለው ነው፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ትርክቱን ለመቀየር ጥሩ አጋጣሚ ስለሚሆን ነው፡፡

ለአብነት የኢትዮጵያ ተቀናቃኝ የሆኑ አካላት ይህን አባባል ወስደው መልሰው እኛኑ ገርፈውበታል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አባባሉ የተተረጎመበት መንገድ ስህተት በመሆኑ ነው፡፡ ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› ማለት ምንም እንኳ እንደየአተረጓጎማችን የሚለያይ ቢሆንም፤ በአጭር አገላለጽ ኢትዮጵያ በቂ ውሃ አላት እንደማለት ነው፡፡ ከዚህ ትርጓሜ አኳያ ስናየው ኢትዮጵያ በቂ ውሃ አላት ማለት አያስችለንም፤ አንችልምም፡፡ ምክንያቱም በአገራችን እየተከናወነ ያለውን ስናስተውል በየዓመቱ ድርቅ የሚያጠቃን፣ ዜጎቻችን የሚፈናቀሉብን ብሎም ከብቶች የሚያልቁብንና ከዚህም የተነሳ ከፍተኛ ችግር ውስጥ የምንገባው ውሃ ስለሌለን ነው፡፡

ነገር ግን ከመልካምድራዊ አቀማመጥ አኳያ ሲታይ በከፍተኛ ቦታ ላይ በመሆናችን የተነሳ ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› ሊያስብለን ይችላል፡፡ ይህ ግን በኢትዮጵያ ሁሉም ቦታ ላይ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለአብነት ያህል የአባይ ቤዚንን ብንወስድ ብዙ ውሃ ሊኖር ይችላል፤ እሱ ውሃ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት አገርም ጭምር መሆን የሚችል ነው፡፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን አቀማመጥ ከተፋሰሱ አኳያ ሲታይ ጎረቤት አገሮችም እንዲጠቀሙበት ተደርጎ የተፈጠረ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ከመሬት አቀማመጥ አኳያ ሲታይ ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› መባሏ ሊያስኬድ ይችላል፡፡ ነገር ግን ካለው የውሃ ሀብትና ካለው ፍላጎት አንጻርና ካለው የልማት ፍላጎት አኳያ ሲታይ ግን ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› የሚያሰኝ ሁኔታ የለንም፡፡

ለምሳሌ የአዋሽ ወንዝን ብንወስድ ክረምት ላይ በጎርፍ ሲጠለቀለቅ ይታያል፡፡ በጋ ሲመጣ ደግሞ ድርቅ ነው፡፡ ባሮ አኮቦ እንዲሁ በተወሰነ ደረጃ ጎርፍ ይኖረዋል፡፡ ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ የሚባሉት ወንዞች አካባቢ ደግሞ የሚስተዋለው ከፍተኛ ድርቅ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ኅብረተሰቡ በየዓመቱ ይሰቃያል፡፡ ከኅብረተሰቡ መሰቃየት የተነሳም ብዙ ዋጋ እየከፈልን ነው፡፡ ስለዚህ አገሪቱ ‹‹የውሃ ማማ ናት›› የሚያብስለን ነገር የለም ማለት ነው፡፡

እንደአገር ግን ስናይ በከፍተኛ ቦታ እንደመኖራችን መጠን ከከፍታው የተነሳ ‹ማማ› መባል ካልሆነ በስተቀር መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ሲታይ አባባሉ ሚዛን የሚደፋ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ያለን የውሃ ሀብት ጥቂት በመሆኑ ካለን ፍላጎት ጋር ሲተያይ በፍጹም የሚመጣጠን ባለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ አገራችን ‹‹የውሃ ማማ ናት›› ብለን ከመናገር ይልቅ ኢትዮጵያ ብዙ ውሃ ማልማት የሚያስፈልጋት የውሃ እጥረት ውስጥ ያለች አገር ናት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት እየተባለ ሲነገር የነበረው ትርክት የተሳሳተ ከሆነ በከፍታ ቦታ ከመሆኗ የተነሳ ያላትን ውሃ እንኳ እንደ አገር በአግባቡ ለመጠቀም የሔደችበት ርቀት እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** አስቀድሜ እንደጠቀስኩት እንደ አገር በቂ ውሃ የለንም፡፡ በሌላ በኩል ሲታይ በጣም ብዙ ሕዝብ ደግሞ አለን፡፡ ብዙ መሬትም አለን፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ብዙ ችግሮች አሉብን፡፡ በአንጻሩ ብዙ ወጣቶች ደግሞ አሉን፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙ ፋብሪካዎችን እንፈልጋለን፡፡ ለዚህ ሁሉ ነገር ዋና መሠረቱ ውሃ ነው፡፡

ለምሳሌ ስለፋብሪካ ስናወራ፣ ስለብዙ ወጣትና ብሎም ስለብዙ ተመራቂ ስናነሳ ወደ አዕምሯችን ፈጥኖ ሊመጣ የሚችለው የሥራ ዕድል ነው፡፡ የሥራ ዕድል ደግሞ ሊመጣ የሚችለው ብዙ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ሲኖሩን ነው፡፡ ኢንዱስትሪ እንዲኖር ደግሞ የመጀመሪያው ጉዳይ ኢነርጂ ነው፡፡ ኢነርጂን ለማምጣት ውሃ ያስፈልገናል፡፡ እኛ ለዚያ የሚሆን ውሃ ለጊዜው አለን ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ያንን ለማድረግ ያለንበት የከፍታ ቦታው በራሱ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን አላለማነውም፡፡ ገና ብዙ ማልማት የሚገባን የውሃ አቅም እንዳለን ማሳያዎች አሉ፡፡ ይህ በኢነርጂው አልተጠቀምንበትም ማለት ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በመስኖ ብንወስድ ሰፊ መሬት አለን፡፡ ይሁንና ብዙ ቦታዎች ሳይለሙ ይቆያሉ፡፡ በተለይ በአገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች በጣም ለም መሬት አለ፡፡ እንዲያም ሆኖ በተፈለገው ልክ ማልማት አልተቻለም፡፡ ይህን መሬት ማልማት ያልተቻለው በአካባቢው ዝናብ አለመኖሩ አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአካባቢውም ሰዎች አለመኖራቸው ነው፡፡ ስለዚህ ውሃን መጠቀም ብንችልና ማኅበረሰባችንን ተጠቃሚ ማድረግ ቢቻል በመስኖ ማልማት የሚቻልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡

ለምሳሌ እንደእነገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ሌሎች የአባይ ተፋሰስ ውስጥ የሚገቡ ናቸው የምንላቸው ገባር ወንዞች እዚህ ውስጥ መካተት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ያልለሙ በጣም ብዙ መሬቶችም አሉ፡፡ ያለመልማታቸው ምክንያት ደግሞ ውሃ ባለመጠቀማችን ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የመጠጥ ውሃ ነው፤ ካለው የሕዝብ ብዛት አንፃር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የውሃ ሽፋን ከ62 በመቶ የማይበልጥ ነው፡፡ እሱም ቢሆን የየራሱ ምክንያት ስላለው ከክልል ክልል እንዲሁም ከከተማ ከተማ ይለያያል፡፡ ስለዚህ ውሃውን ተጠቅመን ቢሆን ኖሮ 38 በመቶ የሚሆነው ውሃ ያላገኘው የኅብረተሰብ ክፍል የውሃ እጥረቱ ተቀርፎለት ውሃ ያገኝ ነበር፡፡ ውሃ አለ፤ ሕዝቡ ግን ውሃ እያገኘ አይደለም፡፡ ታዲያ የጎደለው ምንድን ነው ቢባል፤ የጎደለው የፋይናንስ አቅም ነው፡፡ ያለንን ውሃ በአግባቡ በኢነርጂውም ሆነ በመጠጥ ውሃው ዘርፍ አልምተን እንዳንጠቀም የተገዳደረን የፋይናንስ እጦት ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙ ወንዞቻችን የሚጓዙት እንዲሁ በሜዳ እየፈሰሱ ነው፡፡ ብዙ መሬቶቻችን እንዲሁ ጦማቸውን እያደሩ ነው፡፡ ብዙዎቹ ከተሞቻችንም መብራት ከማጣታቸው የተነሳ የሚያድሩት በጨለማ ውስጥ ነው፡፡ መብራትም ውሃ የላቸውም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ያለንን የውሃ ሀብት እንዳንጠቀም የከለከለን ተግዳሮት የፋይናንስ እጥረት ብቻ ነው ብለን ነው እንስፈው?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** የፋይናንስ ብቻ አይደለም፡፡ በእርግጥ የመጀመሪያ የፋይናንስ እጥረት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የተቋማት የማስፈጸም አቅም ማነስ ነው፡፡ አንዳንዴ ፋይናንስ ኖሮ ፕሮጀክቶች በተባለላቸው ጊዜ ማለቅ ሲገባቸው ሲጓተቱ ይስተዋላል፡፡ ለየፕሮጀክቶቹ የተመደበውም ብር ሳንጠቀምበት ቀርቶ ተመላሽ ሲሆንም እናያለን፡፡ ለአብነት ያህል ዋንወሽ የተባለ ፕሮጀክት በብድር አሊያም በድጋፍ ከተለያዩ አበዳሪ አገሮች ይመጣ የነበረው የተጠናቀቀው በተፈለገው ደረጃ ላይ ደርሶልን ወይም አልቆልን አይደለም፡፡ ፕሮጀክቱ ተቋርጧል፡፡ አንዳንዱ ኪሳራ እና ዕዳ ሆኖ የተላለፈው ወደ መንግሥት ነው፡፡ ያንን ደግሞ መንግሥት የግድ ማጠናቀቅ አለበት፡፡ ስለዚህም ወጪው የሚሆነው ከመንግሥት ካዝና ነው ማለት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው? ከተባለ በወቅቱ የነበረን ቁመና ብሎም የነበረን የማስፈጸም አቅም ጥያቄ ውስጥ ስለነበረ ነው፡፡ ዛሬም ተመሳሳይ ሁኔታ በየቦታው እያጋጠመን ነው፡፡

በየክልሉ ያለው የማስፈጸም አቅም ይለያያል፡፡ አንዳንዱ ክልል ጠንካራ አቅም ያለው ሲሆን፣ አንዳንዱ ክልል ደግሞ ብዙ ይቀረዋል፡፡ ጠንካራ ናቸው የምንላቸው ራሳቸው ጥንካሬያቸው የተዥጎረጎረ ነው፡፡ ቀጣይነት የለውም፡፡ በተለያየ ጊዜ የሰዎች መቀያየር ብሎም የባለሙያዎች ፍሰት እንዲሁም የሎጅስቲክ ሁኔታ ተደማምሮ ብቃትን የሚፈታተን ይሆናል፡፡

እንደ ፖሊሲ በፊት የነበረው አንደኛ ጉዳይ ውሃ የማልማቱ ሥራ ይቀርብ የነበረው ወደመንግሥት ብቻ ነው፡፡ ይህንንም እንደ አንድ ፈተና ማየት ይቻላል፡፡ የግል ባለሀብቱ ወደዚህ ዘርፍ ቢመጣ ውሃውን በአግባቡ ይጠቀምና መንግሥትን ያግዛል፡፡ ያለንን ሀብትም በአግባቡ በመጠቀም የዜጎችን ሕይወት ማሻሻል እንችላለን፡፡ ሀብቱን እንዳንጠቀም ያደረገን የእነዚህ ድምር ውጤት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ውሃ ሙሉ ስሙሉ የላትም የሚል እምነት የለም፣ ከዚህ አንጻር በኢነርጂው ዘርፍስ ባለን አቅም በአግባቡ መጠቀም ያልቻልነው ለምንድን ነው?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** አንዱ ውሃን ለኢነርጂ ስንጠቀም እኛ ማየት የሚገባን ወንዙ ስላለን ብቻ አይደለም፡፡ በፖሊሲ ውስጥ ያሉ ሥራዎች አሉ፡፡

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

ለምሳሌ በየተፋሰሱ ያሉ ሃይድሮፓወር የማመንጨት አቅም ያላቸው ቦታዎች ተለይተው ስለተቀመጡ የመጀመሪያው ሥራ ውሃ መያዝ ነው። ለዚህ ደግሞ ግድብ ያስፈልገናል፤ ያንን ግድብ ከገደብን በኋላ ሲስተሞች መዘርጋት አለባቸው። ማከፋፈያችን ብሎም የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት የግድ ይላል፤ ይህን ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም፤ በየቦታው ደግሞ እንዲደርሱ ማድረግም ሌላው ጉዳይ ነው። ለዚህ ትልቁና ዋናው ተግዳሮት የፋይናንስ አቅም መጠየቁ ነው። እውነት ለመናገር ደግሞ በዚህ ላይ የፋይናንስ አቅም የለንም። ኢትዮጵያ አሁን ባላት ደረጃ ያላትን ውሃ በሙሉ ገድባ ወደዚህ አገልግሎት ለማምጣት ብዙ ፈተናዎች ያሉባት አገር ናት።

ስለዚህ ያለንን የውሃ ሀብት ለማልማት ያስችለን ዘንድ፤ ቁርጠኝነቱ ከመንግሥት ብቻ የሚጠበቅ አይደለም። የግል ባለሀብቱ ከውጭም ከአገር ውስጥም ወደዚህ ዘርፍ በመግባት መሥራት ቢችል ማኅበረሰባችን መብራቱንም ውሃውንም መጠቀም ይችላል። ከዚህም የተነሳ ዜጋው የተሻሻለ ሕይወት መምራት ይችላል።

አሁን ግን ሥራው የመንግሥት ብቻ በመሆኑና መንግሥት ለዚህ አቅም የሌለው በመሆኑ ኢነርጂያችንን በተፈለገው ልክ ማልማት አልቻልንም። ለምሳሌ የኢነርጂ ተደራሽነት ሲታይ አሁን ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር ሲነጻጸር ተጠቃሚው ከ48 በመቶ አይበልጥም። ስለዚህ ወደ 52 በመቶ አካባቢ የሚሆነው ሕዝብ ዛሬም ኢነርጂ የለውም ማለት ነው። በመሆኑም በአገራችን ያለው የኢነርጂ ፍላጎት ትልቅ ነው። ይህንን ትልቅ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የግሉ ባለሀብት ዘርፉን እንዲቀላቀል ብናደርግ የተጠቃሚውን ቁጥር ከፍ ሊያደርገው ይችላል። ምክንያቱም በኢነርጂው ዘርፍ የግል ባለሀብት በጣም ወሳኝ ነው። ከዚህ የተነሳ ፖሊሲያችንንም እየከለስነው እንገኛለን። በፖሊሲያችን ውስጥ የግሉ ባለሀብት መግባትን እንደ አንድ የፖሊሲ አካል አስገብተን እየሠራን እንገኛለን። ስለዚህም ይህ ችግሩን ይፈታል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢነርጂ ለማግኘት እንደ አማራጭ ከምንይዛቸው ነገሮች አንዱ የነፋስ ኃይልን ጨምሮ ሌሎችም ይጠቀሳሉ፤ በዚህ ዘርፍ በመጠቀም ኃይል ለማመንጨት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች እንዳሉም ይታወቃል፤ ይህ ምን ደረጃ ላይ ነው? ከዘርፉ ኃይል ለማመንጨት በሚደረገው ጥረት ያጋጠመ ተግዳሮትና የተፈታበት መንገድም ካለ ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የኢነርጂ አቅሞች የትኞቹ ናቸው ብለን ለይተናቸዋል። አንደኛው በውሃ የሚመነጨው ኃይድሮፓወር ነው። ከዚህ ቀጥሎ ነፋስና ፀሐይ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ደግሞ የእንፋሎት ኃይል አለ። የነፋስና የፀሐይ ኃይልን በምናይበት ሰዓት ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ በነፋስ ኃይል የሚገኝባቸው ቦታዎች በትግራይ ክልል አሸጎዳ፣ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ብሎም ወደ ሱማሌ ክልል አይሻ የሚባሉ አካባቢዎች ናቸው። በትግራይና በአዳማ ያሉት አሁንም ኃይል በማመንጨት ረገድ እየሠሩ ይገኛሉ። አይሻን በሚመለከት ግን ግንባታው አላለቀም። በተወሰነ መልኩ ወደሥርዓቱ (ሲስተሙ) የገባና እያመረተ ያለ ፕሮጀክት ነው። ቢሆንም ያልተጠናቀቁ ጉዳዮች አሉ። ይህ የተቋራጩና በፊት የነበረው የብድር ስምምነት ጋር በተያያዘ (በቦታው የሚሳተፉት የቻይና ተቋራጮች ናቸው) አንዳንድ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ስላሉ ነው። እሱን የማስተካከሉ ሁኔታ ስላለ ጊዜ ሊወስድ ችሏል። በነፋስ የመጠቀም አቅማችን በጣም ትልቅ ነው። በጣም በርካታ ቦታ የነፋስ ኃይል ብንጠቀም ውጤታማ ሥራ ማስመዝገብ እንደምንችል አይተነዋል። የፀሐይ ኃይልንም በተመለከተ በዚያው ልክ ትልቅ አቅም አለን።

አንድ ሊስተዋል የሚገባው ነገር በአሁኑ ወቅት ትልቁን ድርሻ የወሰደው ማለትም ወደ 98 በመቶ ያህሉ በውሃ የሚመነጨው ኃይድሮፓወር ነው። ይህንን በተመለከተ ስብጥሩን ማስተካከል ያስፈልጋል። ኃይድሮፓወርን እየሠራ የኢነርጂ ስብጥሩን ማስተካከል ፀሐዩንም (ሶላሩንም) ሆነ የነፋስ ኃይሉን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል። ከዚህ አኳያ በስፋት መሥራት ይቻላል።

በተለይ ኦፍግሪድ (ኦፍግሪድ ማለት በዚያችው መንደር አሊያም ከተማ ውስጥ ላሉ ማኅበረሰብ የራሱ የሆነ ኢነርጂ ማቅረብ መቻል ማለት ነው) ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰው አቀማመጥ ግን በጣም የተራራቀ በመሆኑ፤ የተነሳ በዋናው ግሪድ (ቋት) ከኃይድሮፓወር ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ቀጣዩ መሆን ያለበትና የምንከተለው ኦፍግሪድ የሚባለውን ሲስተም ነው። ለዚያ ደግሞ የሚሆነው አንደኛው ነፋስ ነው። ሁለተኛው ሶላር ነው። ከዚህ አንጻር በዚህ ዘርፍ ትልቅ እንቅስቃሴ እያደረግን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- አስቀድመው እርስዎ እንደጠቀሱት በአገራችን ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ አሁንም በጨለማ ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህን የሕዝቡን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት በዘርፉ ያለውን ዓለምአቀፍ ተሞክሮ በመውሰድ ባለሀብቶችን ለማስገባት ያልተቻለው ለምንድን ነው? ከዚህ አንጻር በቀጣይ ያቀዳችሁትስ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** ባለሀብቶችን በማስገባቱ ረገድ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ። የመንግሥትና የግሉ ባለሀብት ጥምረት በሚለው ሞዴል ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ባለሀብቶቹ በብዛት ፍላጎት ያላቸው በሶላር ላይ ነው። ለምሳሌ መንግሥትና የግሉ ባለሀብት ጥምረት በሚለው ሞዴል ባለሀብቶች ከገቡበት ዘርፍ አንዱ የእንፋሎት ዘርፍ ነው። ሶላርን በሚመለከት በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባሉበት አንድ ኩባንያ 500 ዋጋ ዋት በሶላር ሊያለማ ፍላጎት አሳይቷል። ይህ አንዱ ማሳያችን ነው፤ ስለሆነም የግሉ ባለሀብት አሁን እያሳየ ያለው ትኩረት ግድቦችን ሠርቶ ኢነርጂ ማመንጨት ሳይሆን ፍላጎቱ በሶላር በነፋስ ላይ ለማልማት ነው።

በተጨማሪ አሁን አሁን ፍላጎት እያሳዩ የመጡት በግሪን ሃይድሮጂን በሚባለው ዘርፍ ላይ ነው። የግሪን ሃይድሮጂን ለማምረት ከፍተኛ የሆነ የታዳሽ ኃይል እንደሚያስፈልግና በዚህም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የታዳሽ ኃይል አማራጭ መኖሩን ተከትሎ ብዙ ባለሀብቶች ወደኢትዮጵያ እየመጡ ይገኛሉ። ይሁንና በተፈለገው ደረጃ ላይ ነው ማለት አያስችልም። ምክንያቱም ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የአገሪቷ ዕጣ ፈንታ እንኳ ያልተወሰነ ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ይህ ባልተወሰነበት ሁኔታ የትኛውም ባለሀብት ደፍሮ መጥቶ በአገሪቷ ላይ መዋዕለንዋዩን የሚያፈስበት ሁኔታ አናሳ ነው። ቀደም ሲል ይህ የሰላም አለመኖር በራሱ ፈተና ነበር። በአሁኑ ሰዓት ግን ችግሩ ተፈትቷል።

በአሁኑ ወቅት እንደገለጽኩት በጣም ብዙ ፍላጎቶች እየተንጸባረቁ ነው። ከዚህ አኳያ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ እያዘጋጀን እንገኛለን። እንዲሁም የፕራይቬት ፓርትነር ፖሊሲም እያዘጋጀን ነው። ከዚህ አንጻር ያለው ጅማሮ ጥሩ የሚባል ዓይነት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር እየተሸጋገረች እንደሆነ ይስተዋላል። ከዚህ አኳያ ለሚደረገው ሽግግር የኢነርጂው ዘርፍ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ እንደሆነ ይታወቃል። በቀጣይ ይህንን አስተሳስሮ ከመሄድ አኳያስ የታቀደው ምንድን ነው?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** አንዱና በጣም ወሳኙ የኢነርጂ ማመንጨት አቅማችንን ማጎልበት ነው። የማመንጨት አቅምን ማጎልበት ማለት ከወንዝ ተጠልፎ የሚኖረን ግድብ ብዙ የኢነርጂ ምርት እንዲኖር የማድረግ ሥራ ነው። በዚህ ረገድ የህዳሴ ግድባችን ትልቅ ለውጥ ያመጣል። አሁን ከኃይድሮፓወር ያለን የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ አራት ሺ 880 ሜጋ ዋት ነው። ህዳሴ ግድባችን ሲያልቅ ይህንን ቁጥር እጥፍ ያደርገዋል። ስለዚህ ይህን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል አንዱ ተግባራችን ነው።

ከዚያ በኋላ ያሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ወሳኝነት ያላቸው ናቸው። አገሪቷ ኢነርጂ በኢነርጂ የምትሆነው ስላመነጨን ብቻ አይደለም። ማከፋፈያዎች ብሎም ማስተላለፊያዎች ላይ የተሻለ ሥራ መሠራትም ይኖርበታል። ታሪፍ መሰብሰብ፣ የዜጎችን ቅሬታ በጊዜ እየፈቱ መሄድ፣ ደንበኞችን እያፈሩ መጓዝ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልና በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት በኩል ያሉት ሥራዎች በተቀላጠፈ መልኩ የሚሠራበትን ብልሃት መዘርጋት እጅግ በጣም ወሳኝነት አለው። ይህን ካደረግን ኢንዱስትሪዎች በራሳቸው ጊዜ ይመጣሉ። በሌላ አገላለጽ ምቹ ቦታ ያገኛሉ ማለት ነው።

በዚህ አጋጣሚ መግለጽ የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኢነርጂ በጣም ርካሽ ነው። ካሉት የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ኢነርጂን በአነስተኛ ዋጋ የምታቀርበው ኢትዮጵያ ናት። ምክንያቱም በመንግሥት ድጎማ ስለሚደረግ ነው። ስለዚህ ይህም ተመራጭ ያደርጋታል። በዚህ አግባብ መጓዝ ከተቻለ ኢንዱስትሪም እየተስፋፋ ይመጣል፤ ኢንዱስትሪ እየተስፋፋ መጣ ማለት ደግሞ በራሱ ግብዓት ፈላጊ ይሆናል። ሁሉም ግብዓት ደግሞ ከውጭ የምናመጣው አይደለም። በብዛት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ መሠረት ግብርና ነው። ያንን ግብርና ደግሞ ወደ ኢንዱስትሪ ማምጣት የግድ ነው።

ለምሳሌ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተብሎ በየቦታው ተሠርተውና ተገንብተው የቆሙ አሉ። አንድም በባለሀብት ፍላጎት ማጣት የቆሙ ናቸው። ሁለትም ኢነርጂ ባለማግኘታቸው ነው። ፓርኮቹ ደግሞ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲሆኑም የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመባል የሚታወቁ ናቸው። ሻሸመኔ፣ ቡልቡላ፣ ነቀምት፣ ቡሬ፣ ኢተያ፣ ኮምቦልቻ እንዲሁም ይርጋለም ላይ ያሉት ግብርና መር የሆነ ግብዓት ይፈልጋሉ። ሲመሠረቱም የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። ለምሳሌ ይርጋለም ያለው እዚያ አካባቢ ቡና እንዲሁም ፍራፍሬ አለ፤ ይህን አሸጎ እሴት ጨምሮ ወደውጭ ገበያ ለማቅረብ ነው።

ቡልቡላና ሻሸሜ አካባቢ ያሉት ደግሞ ጥራጥሬ፣ እንደ ገብስና ስንዴ ላይ ሥራዎችን መሥራት ላይ ነው። በመሆኑም ኢንዱስትሪዎቹ ባለሀብት ይፈልጋሉ፤ ባለሀብት ሲመጣ ደግሞ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይችላል። ለዚህ ሥራ የሚሆኑ ትልልቅ ግብይቶች አሉ። በዚህ አጋጣሚ የሠራናቸው ሥራዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ የሚጀመሩ የኃይል ማመንጫ ግድቦች ካሉ ቢጠቅሱልን፤ እንዲሁም እየተጠናቀቁ ያሉም ካሉ አካተው ቢገልጹልን?**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** አዲስ የሚጀመር የኃይል ማመንጫ ግድብ ለጊዜው የለንም። ትኩረታችን ያሉትን በአግባቡ መጨረስ ላይ ነው፤ ከዚህ ውስጥ አንዱ ትኩረት የሚሻው የህዳሴ ግድብ ነው። ሌሎች ተጀምረው ፍጥነታቸው በተፈለገው ልክ መሄድ ባይችልም እንደ ኮይሻ ዓይነት ግድቦች አሉና እነርሱን የማጠናቀቅ ሥራ ይሠራል። ከእሱ ባሻገር ተጨማሪ ጥናቶች ይሠራሉ። ለምሳሌ በዚህ ዓመት ኃይድሮፓወር ሊሆን የሚችል በተለይ አነስተኛ ግድብ ላይ ጥናት እናደርጋለን። ይህ ብዙ ውድ ላይሆን ይችላል። በጣም አነስተኛ ዋጋ ያለው ነው። አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ለኦፍግሪድ ሊያገለግሉ የሚችሉ ናቸው። ይህ ከኢነርጂ ጋር በተገናኘ ያነሳሁት ነው። ከመጠጥ ውሃ ጋር በተገናኘ ብዙ ከተሞች ላይ ብዙ የውሃ ፕሮጀክቶችን እናጠናቅቃለን ብለን እየሠራን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ሀብታሙ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

**‹‹ያለንን ውሃ በአግባቡ በኢነርጂውም ሆነ በመጠጥ ውሃው ዘርፍ አልምተን እንዳንጠቀም የተገዳደረን የፋይናንስ እጦት ነው››**

# ዓለም አቀፍ



## በጦርነቱ ሳቢያ በርካታ ሩሲያውያን ነፍሰ ጡሮች ወደ አርጀንቲና እየኮበለሉ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ባለፉት ወራት ከ5 ሺህ በላይ ሩሲያውያን ነፍሰጡሮች ዜግነት ለማግኘት ወደ አርጀንቲና መግባታቸውን የአገሪቱ ባለሥልጣናት አስታወቁ።

ከቀናት በፊት ሐሙስ 33 ነፍሰጡር ሩሲያውያን በአንድ በረራ ተሳፍረው ወደ ሀገሪቱ መድረሳቸውም የተገለጸ ሲሆን በተለይም በቅርብ ጊዜ ወደ አርጀንቲና የኮበለሉ ነፍሰ ጡሮች በመጨረሻዎቹ የእርግዝና ሳምንታት ውስጥ መሆናቸው የአገሪቱ የብሔራዊ ፍልሰት ኤጀንሲ ገልጿል።

ቁጥራቸው በተለይም በቅርቡ እያሻቀበ ያለው ኮብላይ ነፍሰጡሮች በዩክሬን ጦርነት ምክንያት መሆኑ የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ዘገባ እየዘገቡ ሲሆን ነፍሰጡሮቹ የአርጀንቲና ዜግነት ለማግኘት ሲሉ ልጆቹን በአርጀንቲና ለመውለድ እንዳቀዱም ነው የታመነው።

ሐሙስ ዕለት በአንድ በረራ ወደ አርጀንቲና ቦነስ አይረስ ከደረሱት 33 ሴቶች መካከል ሶስቱ የያዟቸው የጉዞ ሰነዶች ላይ ችግር በመኖሩም በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የአገሪቱ ብሔራዊ የፍልሰት ኤጀንሲ ኃላፊ ፍሎሬንሺና የተናገሩ ሲሆን ከዚያ በፊት በነበረው በረራ ሶስት ሴቶችም በተመሳሳይ ችግር በቁጥጥር ስር መዋላቸውም ነው የተገለጸው።

እነዚህ ነፍሰ ጡር ሴቶች አርጀንቲና የመጡት ለጉብኝት እንደነበር መጀመሪያ ላይ ተናግረው ነበር። ነገር ግን ቱሪስት መሆናቸውን አመላካች ጉዳዮች አለመኖራቸውን ተከትሎም ለጉብኝት እንዳልመጡም አምነዋል።

ሐሙስ ዕለት በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩት የሶስቱ ሴቶች ጠበቃ በበኩላቸው ሃሰተኛ ቱሪስቶች በሚል ተጠርጥረው ታስረዋል፤ ይህም በአርጀንቲና ሕግ ውስጥ የሌለ ነው፤ ወንጀልም እንዳልሰሩና በሕገወጥ መንገድ ነጻነታቸውን እንደተነጠቁም በመናገራቸው ሴቶቹም ከእስር ተፈትተዋል።

እነዚህ ሴቶች ልጆቻቸው የአርጀንቲና ዜግነት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ ምክንያቱም የአርጀንቲና ፓስፖርት ከሩሲያ ፓስፖርት በበለጠም ነጻነት ስለሚሰጥ ነው ሲሉም ኃላፊዋ ተናግረዋል። የአርጀንቲና ፓስፖርትን የያዙ ዜጎች ወደ 171 አገራት ከቪዛ ነጻ በሆነ መልኩ እንዲጓዙ ያስችላቸዋል። አሁን ባለው ሁኔታም ሩሲያውያን ያለ ቪዛ ወደ 87 አገራት መጓዝ ይችላሉ።

በአርጀንቲና ልጅ በሚወልዱበትም ወቅት ልጆቻቸው ዜግነት የሚያገኙ ሲሆን የወላጆቻቸውን የዜግነት ሂደትም ያፋጥናል።



## አረብ ኢምሬትስ ወደ ሶሪያና ቱርክ በርካታ ቶን ሰብአዊ እርዳታ ላከች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት አረብ እምሬትስ የርዕደ መሬቱ ቀውስ ተከትሎ በርካታ ቶን ሰብዓዊ እርዳታ ወደ ሶሪያና ቱርክ መላኳን ቢቢሲ አስነበበ፡፡

አረብ ኢምሬትስ ከአምስት ቀናት በፊት በአንድ ቀን ውስጥ 117 ቶን የምግብ እርዳታ ወደ ቱርክ እና ሶሪያ መላኳ የሚታወስ ሲሆን በትናትናው እለት ደግሞ 430 ቶን ሰብዓዊ እርዳታ ወደ ሶሪያ መላኳ የአገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ሚኒስቴሩ በዛሬው እለት እንዳስታወቀው፤ ወደ ሶሪያ ደማስቆ በርካታ ካርጎ አውሮፕላን በረራዎችን በማድረግ 430 ቶን ሰብአዊ እርዳታ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ለሶሪያ ከተላኩት የእርዳታ ቁሳቁስ መካከልም 20 ቶን መድሃኒትና የህክምና ቁሳቁስ፣ 155 ቶ ምግብ ነክ ቁሳቁሶች እንዲሁም 2 ሺህ 58 መጠለያ ድንኳኖችን መሆናቸው መከላከያ ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

የአረብ ኢሚሬስት ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህንያን፤ በቱርክ እና በሶሪያ ያጋጠመውን ርዕደ መሬት ተከትሎ ድጋፍ የሚያደርግ የኦፕሬሽን ኮማንድ እንዲቋቋም ማዘዛቸው ይታወሳል። ይህንን ተከትሎም የተቋቋመው ኮማድ በሶሪያ እና በቱርክ በተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ በማቅረብ ላይ ይገኛል።

በደቡባዊ ቱርክ እና ሰሜናዊ ቱርክ እንዲሁም በሶሪያ ከአምስት ቀናት በፊት ባጋጠመ ከባድ ርዕደ መሬት አደጋ የሟቾች ቁጥር በየዕለቱ በማሻቀብ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቱርክ ብቻ እስከ ዛሬ ድረስ የሟቾች ቁጥር ከ21 ሺህ በላይ የደረሰ ሲሆን፤ በሶሪያም ከ3 ሺህ በላይ ሰዎች ሞተዋል፤ በድምሩም እስካሁን የሞቱ ሰዎች ቁጥር 25 ሺህ ገደማ ደርሷል።

ይህ አደጋም በመሰረተ ልማት ላይ ባደረሰው ጉዳት ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኪሳራ እንደሚያደርስም ተገምቷል።

ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት

በስጥሻቸው ልዑልሰገድ

የራሱን መብት እስከብሮ የሌላውን መብት የሚያከብር ዜጋ ለማፍራት መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ዜጋ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግም ዋናውና በቀላሉ ሁሉም ዜጎች ጋር መድረስ የሚቻልበት መንገድ ትምህርት ነው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ስልጠና መግለጫ እንደሚያስቀምጠው የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ስልጠና በሙሉ በሁሉም የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን የሚመለከት የዕድሜ ልክ ሂደት መሆኑንና ይህም ከሙዓለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች መድረስ ያለበት የሰብዓዊ መብት ጥያቄ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርም ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችለውን የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለማካተትና ለማጠናከር የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር ተፈራርመዋል።

ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም የተፈረመው ስምምት የሰብአዊ መብቶች እሴቶችን ወደ ማህበረሰቡ ከማስረፅ አኳያ ተደራሽነትን በመጨመር በኢትዮጵያ ዘላቂና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሰብዓዊ መብቶች ባህልን ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ስለእኩልነት፣ ሰብዓዊ ክብር፣ ፍትሐዊነት፣ ሰላም፣ መከባበርና ኃላፊነት እውቀት በማዳበር የሰብዓዊ መብቶች እሴቶች መግለጫ የሆኑ የባህሪና የአመለካከት ለውጦችን እንዲያመጡ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

ስምምነቱ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ በአግባቡ እንዲካተት፣ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ በጋራ መስራትን፤ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት በተጓዳኝ የትምህርት መንገዶች በተለይም በክለቦች እና በሌሎች የማስተማሪያ ማዕቀፎች ውስጥ በማካተት ለተማሪዎች የሚደርስበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ከሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራት የሚሉ ዝርዝር አላማዎችን ያካተተ ነው፡፡

በመግባቢያ ስምምነቱ መሠረት ሁለቱም ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው የሥራ ድርሻ የሚኖራቸው ሲሆን በዚሁ መሠረት የትምህርት ሚኒስቴር የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትን አመቺ በሆኑ የትምህርት ዓይነቶች በተለይም በግብረ-ገብና በዜግነት ትምህርቶች በግልፅ እና ትርጉም ባለው ደረጃ መካተታቸውን ለማረጋገጥና በተጓዳኝ የትምህርት ዘርፎች እንዲሰጥ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ሥራ ላይ ያሉ ሥርዓተ ትምህርቶችና የስልጠና መጻሕፍት ይዘት በተሟላ መንገድ የሰብዓዊ መብቶችን ፅንሰ ሃሳብና መርሆችን እውቀት የሚያስጨብጥ መሆኑን ለመረጋገጥ እና በየአመቱ ኮሚሽኑ የሚያካሂደውን ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምስለ ፍርድ ቤት(moot court) ውድድር በተመለከተ አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ እንደሚሠራ በስምምነቱ ተካቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በበኩሉ በዋናነት ከትምህርቱ በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤ ለሰብዓዊ መብቶች ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ ደጋፊ ጽሑፎች የሚገኙበት የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) የሚያዘጋጅ ሲሆን ትምህርት ቤቶች በመደበኛውና በተጓዳኝ ሥርዓተ ትምህርቶች ሰብዓዊ መብቶችን በማስረፅ የእለት ተለት የትምህርት ሂደቱ አካል አድርገው የሚሰሩ እንዲሆኑ ለመደገፍ እና በየአመቱ የሚካሄደውን ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምስለ ፍርድ ቤት ውድድር አጠናክሮ ለመቀጠል ተስማምቷል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በስምምነቱ መፈራረሚያ ሥነሥርዓት ወቅት፤ ሰላም ሊመጣ የሚችለው ሰብዓዊ መብቶች ሲከበሩ ነው ያሉ ሲሆን፤ ለዚህም መብትና ግዴታውን መለየት የሚችል ማህበረሰብ መፍጠር ይገባል፤ ለዚህ እውን መሆን ስምምነቱ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ገልፀዋል።



በስምምነቱ መፈራረሚያ ሥነ-ሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ "የሰብዓዊ መብቶች እሴቶችንና መርሆችን ተገንዝቦ በእለት ተለት ግንኙነቱና በባህሪው የሚያናፀባርቅ ትውልድ መፍጠር፤ በመከባበር፣ በመቻቻልና በመግባባት በሰላም አብሮ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብን ለመገንባት የሚያስችል እርምጃ ነው" ብለዋል፡፡

ሀገራችን የሰብአዊ መብቶች ፈተና ተፈትና ወድቃለች፡ ፡ በሀገራችን ያለው መጠነ ሰፊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ በየቦታው የምንመለከታቸው ዘርፈ ብዙ የመብት ጥሰቶች የሰብዓዊ መብት ፈተናን የወደቅን መሆኑን የሚያመለክቱ በመሆናቸው መፍትሄ ልንሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህንን ልንፈታ የምንችለው ደግሞ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በምንጀምረው መጠነ ሰፊ የትምህርት ሥርዓቱን የመፈተሽና የማሻሻል ሂደት ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት እንዲካተት በማድረግ ነው፡፡ በቅርቡም ወደ ሥራ የሚገባ ሲሆን ሥራው መጠነ ሰፊ ሥራ ነው በመሆኑ በአጭር ጊዜ ለውጡን ማየት የማይቻልበት ሥራ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች የዚህ ዓይነት ፀባይ ያላቸውና የረጅም ጊዜ ራዕይ የሚጠይቁ ናቸው በማለት አብራርተዋል፡፡

ስምምነቱን የተፈራረሙት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ ሲሆኑ በፊርማ ሥነሥርዓቱ ላይ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌና ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮና ጨምሮ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ራኬብ መሰለ እንዲሁም የሁለቱ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በፌዴራል ህገ መንግሥቱ መሠረት ነፃ ፌዴራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብዓዊ መብቶች ማስፋፋት፣ መከበርና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች ተቋም ነው፡፡

# ስፖርት



# አሰላ በፕሪሚየርሊግ ወካይ ክለብ እንዲኖራት የተያዘው ውጥን

**አስማማው ግዛው**

አሰላ ከኢትዮጵያ ከተሞች የምትለየው የበርካታ ብርቅዬ አትሌቶች መናኸሪያ በመሆን ነው። የኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮኖችን በብዛት በማፍራት የሯጮች ምድር ከተሰኘችው አርሲ ዞን የፈለቁ አትሌቶች ወደ ታላቅነት በሚያደርጉት ጉዞ አሰላ መሸጋገሪያ ናት። ስፍር ቁጥር የሌላቸው የዓለም የምንጊዜም ምርጥ አትሌቶች ከዚህች ከተማ ተነስተው ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች ከማስጠራት ባሻገር የዓለም አትሌቲክስ ጌጥና ድምቀት ሆነዋል።

አሰላ በአትሌቲክሱ የገነባችውን ከፍ ያለ ስም በእግር ኳሱም ለመድገም ደፋ ቀና በማለት ላይ ትገኛለች። ከተማዋ በእግር ኳሱ በፕሪሚየር ሊግ ደረጃ ተወካይ ክለብ እንዲኖራት ለማድረግ ጠንካራ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኙ የአሰላ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ገልጿል። ቢሮው ከተማዋ በእግር ኳሱ ከአምስት ዓመታት በፊት መቀመጫውን አሰላ አረንጓዴው ስቴድየም ያደረገው ሙገር ሲሚንቶን ዓይነት ተወካይ ክለብ እንደነበራት ይታወቃል።

አሰላ በአሁኑ ወቅት በፕሪሚየር ሊግ ደረጃ የሚመጥን ክለብ በስሟ እንዲኖራት በመገንባት ላይ የሚገኝ ቡድን እንዳለ ተጠቁሟል።

የአሰላ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በዶ ዳባ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለፁት፣ አሰላ ከተማን እንዲወክል የተቋቋመው አዲስ ክለብ ከፍተኛ የበጀት ችግር ያለበት ቢሆንም ይህን ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል።

ክለቡ ያለበት የበጀት ችግር ብቻ እንዳልሆነና የአመራርና ሌሎች ውስጣዊ ችግሮችም እንዳሉበት የጠቆሙት የቢሮው ኃላፊ፣ «አንድ ክለብ የእኔ ነው ብሎ ትኩረት ከተሰጠውና በጀት ከተያዘለት የመቀጠል ተስፋው ትልቅ ነው» ይላሉ። የአሰላ ከተማ አትሌቲክሱ ላይ ትኩረት በማድረግ እየሠራች እንደምትገኝ ያስታወሱት አቶ በዶ ከአምና ጀምሮ በእግር ኳሱም ብዙ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል። ካለፈው ዓመት ጀምሮም ባለሀብቶችን በማሰባሰብና ኮሚቴ በማዋቀር የተከናወኑ ሥራዎች ለውጥ እያመጡ በመሆኑ ቢሮ የእግር ኳስ ቡድኑን ለማጠናከር የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

አሰላ ጠንካራ የእግር ኳስ ቡድን ኖሯት በፕሪሚየር ሊግ እንድትወከል ከታዳጊዎች ጀምሮ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። በዚህም በከተማዋ ከስምንት የሚበልጡ የታዳጊ እግር ኳስ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን የቢሮው ኃላፊ ጠቁመው፣ እነዚህን ፕሮጀክቶች በማጠናከር ከተማዋ በከፍተኛ ደረጃ የሚወዳደር ክለብ እንዲኖራትና የታዳጊ ፕሮጀክቶችም ልፋት እንዳይባክን ከከተማው አስተዳደር ጋር በመነጋገር በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እግር ኳስ ክለቡ ባለፈው የውድድር ዓመት በአንደኛ ሊግ ተወዳድሮ በአንደኝነት መጨረስ የቻለ ሲሆን፣ በዘንድሮ የውድድር ዓመትም በሁለተኛ ሊግ በመወዳደር ላይ እንደሚገኝ ታውቋል።

ያም ሆኖ በክለቡ ውስጥ ያለው ችግር በመንግሥት ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ሕዝቡን የማስተባበር ሥራም በመሰራት ላይ መሆኑም ተገልጿል። በዚህም በከተማዋ ከሚገኙ ባለሀብቶች ጋር በመተባበር በከንቲባው እውቅና ከተለያዩ ምሁራን ኮሚቴ ተቋቁሞ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው።

«ወደፊትም ብዙ ችግሮች እንደሚመጡ እናውቃለን የሚመጣውን ችግር በመቋቋም ክለቡን ወደ ፕሪሚየር ሊግ እናሳድጋለን» ያሉት አቶ በዶ፣ ክለቡ አሁን ካለበት ሁለተኛ ሊግ በሂደት ወደ ፕሪሚየር ሊግ ቢያድግ በርካታ ተግዳሮቶች ሊገጥሙት እንደሚችሉ ስጋታቸውን አስቀምጠዋል። ሊገጥሙ ለሚችሉ ችግሮች እራን ከወዲሁ ማዘጋጀት እንደሚገባም አክለዋል።



**አሰላ ከተማ በትልቅ ደረጃ የሚወዳደር ክለብ እንዲኖራት ጥረት እየተደረገ ነው፣**

ክለቡ በትልቅ ደረጃ ተፎካካሪ ለመሆን ብዙ ተጫዋቾችን ማስፈረምና ደመወዝ መክፈል ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ጠንካራ መሠረት ያለው በጀት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ከከተማዋ ከንቲባና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክለቡን ሕዝባዊ መሠረትና ድጋፍ እንዲኖረው ከወዲሁ በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ አሁን የተጀመረው እንቅስቃሴም ተስፋ ሰጪ እንደሆነ የቢሮው ኃላፊ አብራርተዋል።

በሰው ኃይል በኩል ክለቡን የማጠናከር ሥራም የተጀመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ሁለት ባለሙያዎች እስከ ዓመቱ መጨረሻ በኮንትራት ተቀጥረው ክለቡን በማገልገል ላይ እንደሚገኙ ታውቋል።

«እግር ኳስ ሲባል ቀላል ይመስላል፣ ከባዱ ነገር እግር ኳስን ማሳደግ ነው። እግር ኳስ እንዲያድግ አጀንዳ አድርገን ልንሠራ ይገባል» ያሉት አቶ በዶ፣ እንደ ኦሮሚያ ክልል ለስፖርቱ ትኩረት አልተሰጠም ባይ ናቸው። ስለዚህም የመንግሥት ድጋፍና በጀት ከሌለ የስፖርት ቢሮ ብቻ በራሱ የጀመረው ጥረት ከግብ ስለማይደርስ የሚመለከተው አካል ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ገልጸዋል።


## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ማስታወቂያ ል/ክ/ከ/ወ/10/ፋ/ጽ/ቤት

### የግዥ መለያ ቁጥር 03/2015

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት ለወረዳው ጽ/ቤቶች ለ2015 በጀት ዓመት በሎት የተጠቀሱትን ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ ሕጋዊ አቅራቢዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ አቅራቢዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡

| የሎት ምድብ | የጨረታ ማስከበሪያ CPO |
|---|---|
| ሎት.1. የወረፋ ማስያዣ ማሽን ዕቃ ግዥ | 10,000.00 |
| ሎት.2. የጽሕፈት መሳሪያ ዕቃ ግዥ | 5,000.00 |
| ሎት.3. የደንብ ልብስ ግዥ | 5,000.00 |
| ሎት.4. ፈርኒቸር ዕቃ ግዥ | 10,000.00 |

በዚሁም መሠረት፡-

1. ተጫራቾች ሕጋዊ የ2015 የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያየላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች TIN.NO ተመዝጋቢ የሆኑና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና በመንግስት ግ/ን/ኤጀንሲ ድረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ ሕጋዊ የTIN እና VAT ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ጥቃቅንና አነስተኛ ተጫራቾች ካደራጃቸው ባለሥልጣን ደብዳቤ የሚመጡት በአምራችነት የተደራጁበትን ደብዳቤ በማምጣት የጨረታ ሰነድ በነፃ በመውሰድ 3 ፐርሰንት ቅናሽ የሚደረግላቸው እራሳቸው ላመረቱት ዕቃና ቫሊው አድ ላደረጉት ዕቃ ብቻ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ/CPO/ ከጨረታ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የሥራ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 100.00/ አንድ መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የግዥ ቡድን መሪ ቢሮ በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ።
6. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የሥራ ቀናት በወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቢሮ ለጨረታ ለተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
7. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ11ኛው ቀን 2፡30 ታሽጎ በዕለቱ ከቀኑ 3፡00 በወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት በመንግስት ግዥ ቢሮ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆኑ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩበት ሎት የተሟላ የፍላጎት መግለጫ እና ሳምፕል ማዘጋጀትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ለእያንዳንዱ ቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።
10. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መሥሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. ለጨረታ ከቀረቡት ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ጽ/ቤቱ እስከ 20 ፐርሰንት ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
13. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

- .ለተጨማሪ ማብራሪያና ጥያቄ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጸ/ቤት የመንግስት ግዥ ቢሮ ቁጥር 0115574351/0115574176 በመደወል ወይም ቅ/ልደታ ቤ/ክርስቲያን ጀርባ አዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ አጠገብ ቢሮ በአካል በመቅረብ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**በልደታ ክ/ከተማ የወረዳ 10 ፋይናንስ ጽ/ቤት**